አዲስ ዘመን
እናድ
እሁድ 83ኛ ዓመት ቁጥር 146 ጥር 26 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


ፎቶ፡- ዳኜ አበረ


# “በኢትዮጵያዊ አንድነቱ የፀና፤ ክንደ ብርቱ ሠራዊት ስለገነባን ፈተናዎችን በጀግንነት መመከት ችለናል”

- የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ

ጌትነት ምህረቴ

ሁርሶ፡- በኢትዮጵያዊነቱ አንድነቱ የፀና ክንደ ብርቱ ሠራዊት ስለተገነባ ሀገራችን የገጠማትንና እየገጠማት ያለውን ፈተና ሁሉ በጀግንነት መመከት ችለናል ሲሉ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ ገለጹ።

በሁርሶ ኮንታጀንት ማሰልጠኛ ማዕከል የአንድነት ኮርስ የመኮንኖች ምረቃ ሥነ-ሥርዓት ትናንት ሲካሄድ ጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ የገጠማትንና እየገጠማት ያለውን ፈተና ሁሉ በጀግንነት መመከትና ሀገራችንን ማጽናት የቻልነው በኢትዮጵያዊነቱ የጸና አንድነቱ ጠንካራ ክንደ ብርቱ ሠራዊት በመገንባታችን ነው።

“ በኢትዮጵያዊ አንድነቱ...ወደ ገጽ 5 ዞሯል


በለጠ ሞላ (ዶ/ር)

## “ኢኮኖሚያችን ላይ አደጋ ለደቀኑ የሳይበር ስጋቶች ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል”

- በለጠ ሞላ (ዶ/ር) የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር

መዓዛ ማሞ

አዲስ አበባ፡- በመሠረተ ልማትና በኢኮኖሚያችን ላይ አደጋ ለደቀኑ የሳይበር ደህንነት ስጋቶች ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል ሲሉ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር በለጠ ሞላ (ዶ/ር) ተናገሩ።

“በኢኮኖሚያችን ላይ...ወደ ገጽ 5 ዞሯል



## ግንባታቸው ሙሉ በሙሉ የተጠናቀቁ ሦስት ሺህ 452 ቤቶች ለጨረታ ሊቀርቡ ነው

መስከረም ሰይፉ

አዲስ አበባ፡- ግንባታቸው ሙሉ በሙሉ የተጠናቀቁ ሦስት ሺ 452 የመኖሪያና የንግድ ቤቶችን ለጨረታ ሊያቀርብ መሆኑን የአዲስ አበባ ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን አስታወቀ፡፡

የኮርፖሬሽኑ ዋና ዳይሬክተር አቶ ሽመልስ ታምራት ትናንት በሰጡት መግለጫ እንዳመለከቱት፤ ኮርፖሬሽኑ ግንባታቸው ሙሉ ለሙሉ የተጠናቀቁ ሦስት ሺ 146 የመኖሪያ ቤቶችና 306 የንግድ ሱቆች በድምሩ ሦስት ሺህ 452 ቤቶች መሆናቸውን አብራርተዋል፡፡

ኮርፖሬሽኑ በከተማዋ እየጨመረ የመጣውን የነዋሪዎች የመኖሪያ ቤት ችግር ለመቅረፍ የተለያዩ አማራጮች ይዞ እየሰራ ይገኛል ብለዋል።

መንግሥት በባንክ በተገኘ የቦንድ ብድር የጋራ መኖሪያ ቤቶችን እየገነባ ለነዋሪው ሲያቀርብ መቆየቱን አስታውሰው፤ የመኖሪያ ቤት አቅርቦት ችግሩ በመንግሥት ብቻ የሚፈታ ባለመሆኑ የግል ባለሀብቱን በማስተባበር ጭምር ነዋሪው ቤት የሚያገኝበት አሰራር መፈጠሩን ገልጸዋል፡፡

ግንባታቸው ሙሉ በሙሉ...ወደ ገጽ 5 ዞሯል













## በዓላትን በሰላም ለማክበር የተሠራውን ሥራ በመሪዎች ጉባኤና በዓድዋ በዓል መድገም ይገባል

- ለሰላም ሠራዊት አመራሮችና አባላት ዕውቅና ተሰጠ

ገጽ 5






ዜና

# የጥቁሮች ታሪክ ሲታሰብ የእጅ አዙር ቅኝ ግዛትን በሚያስቀር መልኩ ሊሆን ይገባል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- የጥቁሮች ታሪክ መታሰቢያ ወር ሲከበር የእጅ አዙር ቅኝ ግዛት አስተሳሰብን በሚያስቀርና አንድነትን በሚያጎለብት መልኩ መሆን እንዳለበት ምሁራን ገለጹ፡፡

በዓመቱ የካቲት ላይ የሚከበረው የጥቁሮች ታሪክ መታሰቢያ ወርን አስመልክቶ በተዘጋጀው የፓናል ውይይት የተሳተፉት የታሪክ ምሁርና ተመራማሪው አየለ በከሬ (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ የጥቁሮች ታሪክ ሲታሰብ አንድነትን በሚያጎለብትና የእጅ አዙር ቅኝ ግዛት አስተሳሰብን በሚያስቀር መልኩ ሊሆን ይገባል፡፡

አፍሪካዊያን በባህል በቋንቋ እንዲሁም በአኗኗር ዘዬ ጠንካራ ግንኙነት አላቸው ያሉት ዶክተር አየለ፤ ይህንን በማጎልበትና ለጥቁር ሕዝቦች ዋጋ የከፈሉትን በማሰብ ፈለጋቸውን መከተል ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

መታሰቢያ ወሩ በውይይት መድረኮች መከበሩ ለወደፊት አላስፈላጊ የቅኝ ግዛት አስተሳሰቦችን ለማስወገድ ያግዛል ያሉት የታሪክ ተመራማሪው፤ አፍሪካዊያን ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም ፖለቲካዊ ግንኙነታቸውን በማሳደግ ነጻነታቸውን ማወጅ ይገባቸዋል ብለዋል፡፡

እንደ ዶክተር አየለ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ ለመላው የጥቁር ሕዝቦች ነፃ መውጣት ከፍተኛ ድርሻ ነበራት፤ ይህን ድርሻዋን በተለያዩ መስኮችም እያሳደጉ መሄድ ይገባል።

የፖሊሲ አማካሪና የኢኮኖሚ ሙሁሩ ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ የጥቁሮች ታሪክ ሲታሰብ አንድነት በማጎልበትና የእጅ አዙር ቅኝ ግዛት አካሄዶችን በተለያዩ ትብብሮች የሚሻሩበትንም መንገድ ማየት እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል።



አየለ በከሬ (ዶ/ር)



ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ (ዶ/ር)

ፓን አፍሪካኒዝም ለአፍሪካውያን ነፃነት ያሳደረው አዎንታዊ አስተዋጽኦ ቀላል አይደለም ያሉት ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፤ በአህጉሪቱ ጠንካራ ኢኮኖሚ ተባብሮ መገንባት ካልተቻለ ደግሞ የአፍሪካን ነፃነትን ሙሉ በሙሉ ለማወጅ አስቸጋሪ እንደማይሆን ተናግረዋል፡፡

እንደ ዶክተር ገለጻ፤ አፍሪካ ለኢንቨስትመንት መዳረሻ ምቹና ቀዳሚ ናት፤ የተፈጥሮ ሀብቶቿንና ዕውቀትን በማስተሳሰር የተሻለ መስራት የሚቻልበትን አማራጭ ማስፋት ይገባል።

በኢትዮጵያ የዛምቢያ ኤምባሲን ወክለው የተገኙት ሚስተር ናዋ ሲቦንጎ በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ ለአፍሪካና ለመላው የጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ትግል አርዓያ መሆኗን ጠቁመው፤ የጥቁሮች ወር በየጊዜው መታሰቡ ለአፍሪካውያን አንድነትና ነፃነት ጉዳዮች ላይ የበለጠ ትብብር ለማድረግ ያግዛል ብለዋል፡፡

መላው አፍሪካዊያን የኢኮኖሚና የንግድ እንዲሁም ፖለቲካዊ ግንኙነታቸው ወደ ላቀ ደረጃ በማድረስ ከዘመናዊ የቅኝ ግዛት አካሄዶች መውጣት እንዳለባቸው መልዕክት አስተላልፈዋል።

ለጥቁሮች ታሪክ መታሰቢያ የሆነው ወርሀ የካቲት፤ ለጥቁሮች ነጻነት የታገሉ አርበኞች፣ የማኅበረሰብ አንቂዎች፣ ተራማጆችና የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾችን ትግል ለመዘከር በየዓመቱ ይከበራል፡፡

# ለበልግ አብቃይ አካባቢዎች የግብርና ሥራ ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር እርጥበት እየተገኘ ነው

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- እየተገኘ ያለው እርጥበት ለበልግ አብቃይ አካባቢዎች የግብርና ሥራ ምቹ ሁኔታ ስለሚፈጥር የማሳ ዝግጅት መደረግ እንዳለበት የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ለኢፕድ በላከው መግለጫ፤ ከጥር መጨረሻ ቀናት እስከ የካቲት 22 ቀን 2016 ዓ.ም ያለውን የአየር ሁኔታ ትንበያ አመላክቷል፡፡

እየተገኘ ያለው እርጥበት የበልግ ወቅት አምራች በሆኑት አካባቢዎች ያለውን የውሃ አቅርቦት ስለሚያሻሽል የማሳ ዝግጅት ማድረግ እንደሚገባ ኢንስቲትዩቱ ገልጿል።

በየካቲት ወር በልግ አብቃይ የሆኑ አካባቢዎች ከመደበኛው በተሻለ ሁኔታ እርጥበት እንደሚያገኙ ጠቁሞ፤ እርጥበቱ ሰብሎችን አስቀድሞ ለመዝራት አመቺ በመሆኑ አርሶ አደሮችና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት አስፈላጊውን የዘር ግብዓት ከወዲሁ ማዘጋጀት እንዳለባቸው አሳስቧል፡፡

ለቋሚ ተክሎች የውሃ አቅርቦት ምቹ ሁኔታ ከመፍጠሩም በተጨማሪ ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንጻር አዎንታዊ ሚና እንደሚኖረው ኢንስቲትዩቱ ገልጿል።

የካቲት ወር በልግ አብቃይ በሆኑ አካባቢዎች በመደበኛ ሁኔታ ዝናብ የሚጀምርበት ሲሆን፤ በተለይ ከወሩ አጋማሽ በኋላ የደቡብ ምዕራብ፣ የደቡብ፣ የሰሜን ምሥራቅ፣ የምሥራቅ፣ የመካከለኛውና አጎራባች የስምጥ ሸለቆ ስፍራዎች የተለያየ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ በመግለጫው ተመላክቷል።

በተለያዩ የበልግ አብቃይ ስፍራዎች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንዲሁም በአንዳንድ አካባቢዎች ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ የትንበያ መረጃው ይጠቁማል፡፡

በላይኛውና መካከለኛው ስምጥ ሸለቆ፣ ኦሞ ጊቤ በላይኛው አዋሽ፣ ባሮ አኮቦ፣ ገናሌ ዳዋ እንዲሁም ዋቢ ሸበሌ ተፋሰሶች ላይ የተሻለ እርጥበት የሚኖራቸው ሲሆን፤ የሚገኘው እርጥበት በተፋሰሶች ውስጥ ያለውን የውሃ ሀብት እንዲሻሻል አዎንታዊ አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ኢንስቲትዩቱ አስታውቋል።

# በኤግዚቢሽኑ ከ30 ሺህ ኩንታል በላይ የሰብል ምርቶች ይቀርባሉ

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- ከጥር 29 እስከ የካቲት 5 ቀን 2016 ዓ.ም በሚካሄደው የኅብረት ሥራ አውደ ርዕይና ሲምፖዚየም ከ30 ሺህ ኩንታል በላይ የሰብል ምርቶች እንደሚቀርቡ የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን አስታወቀ፡፡

“የኅብረት ሥራ ማህበራት ሚና ከገበያም በላይ” በሚል መሪ ቃል የሚካሄደውን አውደ ርዕይና ሲምፖዚየም አስመልክቶ የኢትዮጵያና የአዲስ አበባ ኅብረት ሥራ ኮሚሽኖች ሰሞኑን መግለጫ ሰጥተዋል፡፡

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጌታቸው መለሰ (ዶ/ር) በወቅቱ እንደገለጹት፤ በኤግዚቢሽኑ ከ400 በላይ የተለያዩ ምርቶች የሚቀርቡ ሲሆን ከ30 ሺህ ኩንታል በላይ የተለያዩ የሰብል ምርቶች ይቀርባሉ፡፡

በአውደ ርዕዩ ላይ ከሰብል ምርቶች በተጨማሪ የተለያዩ የእንስሳትና ተዋጽኦዎችና የኢንዱስትሪ ምርቶች በተመጣጣኝ ዋጋ ይቀርባሉ ሲሉ አስረድተዋል፡፡

ዶክተር ጌታቸው እንደተናገሩት፤ በሀገሪቱ 110 ሺህ የኅብረት ሥራ ማህበራት ቢኖሩም እስካሁን ድረስ በሀገሪቱ የገበያ ድርሻቸው 18 በመቶ ነው፡፡

በመርሀ ግብሮቹ ከ250 በላይ አምራቾችና በርካታ ሸማቾች ይሳተፋሉ፤ ይህም ትስስራቸውን በማጠናከር የገበያ ድርሻቸውን ለማሳደግ ዕድል ይፈጥራል ሲሉ ተናግረዋል።

አውደ ርዕዩ የገበያ ሰንሰለቱን በማሳጠር የዋጋ ንረትን ለማረጋጋት ያግዛል ያሉት ዶክተር ጌታቸው፤ በኤግዚቢሽኑ ከ80 ሺህ ኩንታል በላይ የግብርና ምርቶችን ለመገበያያ የሚደረጉ ስምምነቶች እንደሚኖሩ አመላክተዋል።




ጌታቸው መለሰ (ዶ/ር) እና ወይዘሮ ልዕልቲ ግደይ

አውደ ርዕይና ባዛሩ በአዲስ አበባ ኤግዚቢሽን ማዕከል የሚካሄድ ሲሆን፤ ከ100 ሺህ በላይ ሰዎች ይጎበኙታል ተብሎ ይጠበቃል ብለዋል።

ዶክተር ጌታቸው እንደተናገሩት፤ ከአውደ ርዕዩ በተጨማሪ በሚካሄደው ሲምፖዚየ የተለያዩ ጥናታዊ ጽሑፎች ቀርበው ውይይት ይደረግባቸዋል።

የአዲስ አበባ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ኮሚሽነር ወይዘሮ ልዕልቲ ግደይ በበኩላቸው፤ ወደ አዲስ አበባ ከተማ የግብርና ምርቶችን ለማስገባት ውይይት እየተደረገ ነው። ለአንዳንዶቹ ቅድመ ክፍያ ተፈጽሞ ምርቶቹን የማከማቻ ቦታ ተዘጋጅቷል ብለዋል፡፡

በከተማዋ ከስምንት ሺህ በላይ የተለያዩ የኅብረት ሥራ ማህበራት መኖራቸውን የገለጹት ኮሚሽነሯ፤ ከእነዚህ ውስጥ 125ቱ ማህበራት የተለያዩ አገልግሎቶችንና ምርቶችን ይዘው በአውደ ርዕዩ እንደሚቀርቡ ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪ ከ12 በላይ የሸክላና ዕደጥበብ ባለሙያዎች ሥራቸውን እንደሚያቀርቡ ጠቁመዋል። አውደ ርዕይና ሲምፖዚየሙ የኅብረት ሥራ ማህበራት በሀገር አቀፍ ደረጃ ለ10ኛ ጊዜ፣ በአዲስ አበባ ከተማ ለሦስተኛ ጊዜ እንደሚካሄድ ታውቋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ተመራቂ መኮንኖች ራሳቸውን ለትልቅ ታሪክ ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል!

እኛ ኢትዮጵያውያን ነፃነታችንን አስከብረን ዘመናትን መሻገር የቻልነው ለሀገራችን ካለን መተኪያ የሌለው ፍቅር፣ ፍቅሩ በየዘመኑ ከፈጠረው የመስዋዕትነት ገድል እንደሆነ ታሪካችን በስፋት የሚዘክረው እውነት ነው። ለፍትህ እና ለነፃነት ያለን ቀናኢነትም የዚሁ ታሪካዊ እውነታ አካል እንደሆነም ይታመናል።

የቀደሙት አባቶቻችን በየዘመኑ የተነሱብንን፤ በኃይል አስገዝተው የባርነት ቀንበር ሊጭኑብን የተነሱ የውጭ ኃይሎችን አሳፍረው በመመለስ እስከዛሬ ትውልዶች ቀና ብለው የሚሄዱበትን ታሪክ በደማቸው ጽፈው አልፈዋል። በዚህም ኢትዮጵያዊነት የነፃነትና ቀንዲል የሆነበትን ዓለም አቀፍ ትርክት ፈጥረዋል።

በየዘመኑ የነበሩ ትውልዶችም የአባቶቻቸውን ፈለግ በመከተል ሀገር እንደ ሀገር ጸንታ ትቆም ዘንድ፤ የሕይወት መስዋዕትነት ከፍለዋል። የአሁኑም ትውልድ የዚሁ ሀገራዊ ትርክት አካል በመሆን ከፍያለ መስዋዕትነት እየከፈለ፤ ሀገሪቱ ከተጋረጠባት አሁናዊ ስጋቶች በብዙ መስዋዕትነት እየታደገ ይገኛል።

በተለይ ባለፉት ሦስት ዓመታት ሀገር እንደሀገር፤ የህልውና ስጋት ውስጥ በገባችበትና የውስጥና የውጭ ኃይሎች ተናበው እና ተቀናጅተው፤ በጋራ በተንቀሳቀሱበት ወቅት ትውልዱ፤ እንደቀደሙት አባቶቹና አያቶቹ ከፍ ባለ የሀገር ፍቅር ስሜት ፤ ሀገራዊ አደጋዎችን በመቀልበስ አደራ ተረካቢነቱን በተግባር አስመስክሯል።

ከመንግሥት የቀረበለትን ሀገርን የመታደግ ጥሪ ሳያቅማማ በመቀበል፤ በግዳጅ ወረዳዎች ራሱን እያበቃ፤ መስዋዕትነት በሚፈጥረው ጠንካራ ስብዕና ራሱን እያጸና፤ ስለ ሀገሩ ያለውን የማይናወጥ አቋም አሳይቷል። በሀገር ጉዳይ መደራደር እንደማይቻል እራሱን ለመስዋዕትነት በማቅረብ ጭምር በተጨባጭ አስመስክሯል።

በሀገር ጉዳይ ላይ የማይናወጥ አቋም ከፍ ያለ መስዋዕትነት በሚጠይቁ የግዳጅ ቀጣናዎች በመዝለቅ ለሕይወቱ ሳይሳሳ፤ ሀገርን በመታደግ የራሱን ታሪክ በደሙ ጽፏል፡፡ የአባቶቹ ልጅ በመሆን፤ የተንሰላሰለው የትውልዶች የጀግንነት ታሪክ አካል እንደሆነም አረጋግጧል።

መንግሥትም ባለፉት ጥቂት ዓመታት የሀገሪቱን የመከላከያ ኃይል አቅም በሁለንተናዊ መልኩ ለማሳደግ እየሄደበት ያለው ስትራቴጂና እየተመዘገበ ያለው ስኬት የዚሁ እውነታ አንድ ማሳያ ተደርጎ የሚወሰድ ነው። በቀጣይም የሠራዊቱን አቅም ለማሳደግ የሚደረጉ ጥረቶች መሠረታቸው ይኸው ትውልዱ ለሀገሩ በክብር ለመሰዋት ያሳየው ቁርጠኝነት እንደሚሆን ይታመናል።

ትናንት የመከላከያ ሠራዊቱ ፈተናዎች ውስጥ በነበረበት ወቅትም ሆነ አሁን ደግሞ የመከላከያ ሠራዊቱን አቅም ለማሳደግ ሠራዊቱን በስፋት እየተቀላቀለ፤ የተለያዩ ሥልጠናዎች እየወሰደ፤ ራሱን ለግዳጅ ዝግጁ እያደረገ ያለው ወጣት ትውልድ የዚህ እውነታ አካል ነው።

ሕገመንግሥቱንና ሕገመንግሥታዊ ሥርዓቱን ከመጠበቅ አንስቶ፤ ጽንፈኛ አስተሳሰቦች እንደሀገር የፈጠሩብንን የሰላም እጦት በመቀልበስ ሕዝባችን በሰላም ወጥቶ የሚገባበትን፤ የዕለት ተዕለት ሕይወቱን ያለ ስጋት የሚመራበትን ሀገራዊ አውድ ከመፍጠር አኳያ ብዙ የሚጠበቅበትና ሕዝባችንም ተስፋ የሚያደርግበት ነው።

ከዚህም ባለፈ ታሪካዊ ጠላቶቻችን ሆኑ፤ ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ከፍ አድርገን ከያዝናቸውን ትላልቅ ሀገራዊ ራዕዮቻችን ጋር በተያያዘ ሊያጋጥሙን የሚችሉ ስጋቶችን በመቀልበስ፤ እንደ ሀገር ብሩህ ነገዎችን ሠርተን አዲስ የታሪክ ትርክት ለመፍጠር ለጀመርነው ሀገራዊ ንቅናቄ መድህን ነው።

ይህ የሀገርን ህልውና እና ተስፋ፤ የሕዝብን ሰላም ለማስከበር በተለያዩ ሙያዎች በመከላከያ ሠራዊቱ ውስጥ በስፋት እየተካተተ፤ እየሰለጠነና ራሱን እያበቃ ያለ ትውልድ፤ የሀገርን ህልውና አደጋ ውስጥ የከተቱ ትናንቶች በሁለንተናዊ አቅማቸው በድጋሚ እንዳይከሰቱ ማስተማመኛ ሀገራዊ አቅም ነው።

ቀደም ባሉት ጊዜያትም ሆነ ትናንት በሁርሶ ኮንቲጀንት ማሰልጠኛ ማዕከል/ የኢትዮጵያ ወታደራዊ አካዳሚ ሰልጥነው የተመረቁ ዕጩ መኮንኖችን፤ ራሳቸውን የአንድ ትልቅ የተንሰላሰለ ታሪክ አካል አድርገው ማየት፤ ራሳቸውን ለታሪክ ሠሪነት ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## 24/7 የሚፋለሙበት የሳይበር ግንባር...! ?

**በቁምላቸው አበበ ይማም ( ሞሼ ዳያን )**

በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ አጋማሽ እንደ ሀገር ከተሰነዘሩ 4 ሺህ 623 የሳይበር ጥቃት ሙከራዎች 4 ሺህ 493 ያህሉን ማክሸፍ መቻሉን፤ የኢንፎርሜሽን መረብ አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር ሰለሞን ሶካ ገልጸው፤ ከተቃጡ ጥቃቶች ውስጥም 4 ሺህ 493 የጥቃት ሙከራዎች ወይም 98 ነጥብ 56 በመቶውን ማክሸፍ ተችሏል።

ከሳይበር ጥቃት ሙከራ 130 ያህል መከላከል ሳይቻል መቅረቱን ጠቁመው፤ በመከላከል ሥራው ሀገሪቱ ላይ ሊደርስ የነበረ ከ10 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር በላይ ኪሳራ ማዳን መቻሉን፤ የከፍተኛ አደጋ ደረጃ ያላቸው የሳይበር ጥቃት ሙከራዎች ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸሩ በ115 በመቶ መጨመራቸውንም ጠቁመዋል።

የሳይበር ጥቃት ኢላማ የተደረጉ ተቋማት አብዛኛዎቹ የፋይናንስ ተቋማት፣ የፀጥታና ደኅንነት ተቋማት፣ የሚዲያ ተቋማት፣ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች፣ የክልል ቢሮዎች፣ የሕክምና እና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መሆናቸውን፤ የድረገጽ ጥቃት፣ ማልዌር፣ የመሠረተ ልማት ቅኝት፣ የመሠረተ ልማት ማቋረጥ፣ ሰርጎ የመግባት ሙከራ እንደየቅደም ተከተላቸው ከፍተኛ የጥቃት ሙከራ የተደረገባቸው መሆናቸውንም አስረድተዋል።

የሳይበር ጦርነት በአጭሩ እጅግ ጠቃሚ የሆኑ እንደ ፋይናንስ ተቋማት፣ መከላከያ፣ ደህንነት፣ ቴሌኮም ያሉ ተቋማትን የበይነ መረብ የመረጃ ሥርዓቶችን ከጥቅም ውጪ ማድረግ ነው። ስለላ ማካሄድም የጦርነቱ አካል ነው። ራሽያ ዩክሬንን በመውረሯ አኖኒመስ የተባለ የሀክቲቪስቶች ስብስብ በራሽያ ላይ የሳይበር ጦርነት እንዳወጀው፤ በሀገራችን ላይም በህቡዕ የሳይበር ጦርነት የከፈቱብን ኃይሎች መኖራቸው የአደባባይ ምስጢር ከሆነ ሰነባበተ።

የኢትዮጵያ ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ቆየት ባለ አንድ መግለጫው፤ «...መሠረታቸውን ከግብጽ ያደረጉ የመረጃ መረብ ሰርሳሪዎች ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ ተቋማት የመረጃ መረብ መዋቅር ላይ ጥቃት ለማድረግ ሞክረው ነበር ። ...» እንዳለው ተራ ሙከራ ሳይሆን የሳይበር ጦርነት ነው የተከፈተብን። በዋዛ ፈዛዛ ሙከራ በሚል ብቻ የሚታለፍ አይደለም።

በሉዓላዊነታችን፣ በደህንነታችንና በተቋሞቻችን የተቃጣ ጥቃት መሆኑ ሳይቃለል በልኩ ነው መታየት ያለበት። በ21ኛው መክዘ ጦርነት የሚካሄድበት ጦርነት በየብስ፣ በባሕርና በአየር ብቻ ሳይሆን በሳይበርና በስፔስ የታገዘ ስለሚሆን ሀገራት ከዚህ አንጻር ራሳቸውን እያዘጋጁ ነው።

በebs የ" Tech Talk With Solomon " አዘጋጅ ሰለሞን ሙሉጌታ ካሳ" ግርምተ ሳይቴክ " በሚል ርዕስ በ2010 ዓ.ም ለንባብ ባበቃው መፅሐፍ ፤ « የማይታየው ጦርነት» በሚል ምዕራፍ ስር ገፅ 157 ላይ ፤ «...በ21ኛው መክዘ አዲስ ዓይነት ጦርነት ብቅ ብሏል። ጦርነቱ የሚካሄደው በጥይትና በቦምብ ሳይሆን በሀከሮችና በኮምፒውተሮች ነው ። ... ይህ በዓይን የማይታየው የሳይበር ጦርነት/ ዋርፌር / ነው።

«ግብፅን በአየር፣ በየብስ ስንጠብቃት፤ ምን አልባት ባልጠበቅነውና ባልተዘጋጀንበት ስስ ብልታቸው ይሆናል ብላ በገመተችው በሳይበር ግንባር ጦርነት መክፈቷ ከፍ ብሎ ተመልክቷል። የኢትዮጵያ ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ /ኢንሳ/መሠረታቸውን ከግብፅ ያደረጉ የመረጃ መረብ ሰርሳሪዎች በሀገራችን ተቋማት የመረጃ መረብ መዋቅር ላይ ጥቃት ለመሰንዘር ያደረጉትን ሙከራ ማክሸፉ አይዘነጋም። የዘንድሮዎቹ የሳይበር ጥቃቶች መሠረታቸው ከየት እንደሆነ ዋና ዳይሬክተሩ ባይገልጹም ለመገመት ግን አይከብድም።

በኤጀንሲው የወቅቱ መግለጫ መሠረት በሦስት የተለያዩ ቡድኖች አማካይነት የተሞከረው የመረጃ መረብ ጥቃት በሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጫናን ለመፍጠር ያነጣጠረ ነበር። የጥቃቱ ሙከራ ባደረጉት ቡድኖች ላይ አበክሮ ክትትል በማድረጉ በ13 የመንግሥት እና አራት መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማትን ድረ-ገጾችን ኢላማ በማድረግ የተሰነዘሩ ከፍተኛ የመረጃ መረብ የጥቃት ሙከራዎችን በቁጥጥር ስር ማዋል ችሏል። የመረጃ መረብ ጥቃት ሙከራው የተደረገው ሳይበር ሆሩስ ግሩፕ፣ አኑቢስ ዶት ሃከር' እና ሴኪዩሪቲ ባይ ፓስ በተባሉ መረጃ መረብ ሰርሳሪ ቡድኖች ነው።

የጥቃቱ ኢላማ የነበሩት ተቋማት በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የመንግሥት ተቋማት፣ የደኅንነት መሥሪያ ቤቶች እና የግል ድርጅቶች ድረ-ገጽ ላይ መሆኑን ኤጀንሲው በመግለጫው አብራርቷል። ሆኖም ባልተለመደ ሁኔታ በሀገሪቱ ባሉ ተቋማት የመረጃ መረብ ላይ ጥቃት ለማድረስ የሞከሩ ቡድኖች በግልፅ ኃላፊነቱን መውሰዳቸው ግብፅ ለሀገራችን ያላትን ንቀትና እብሪት የሚያስታውስ ሆኖ አግኝቸዋለሁ። ሌላው ኤጀንሲው የሳይበር ጥቃቱ አላማ፤ «በኢትዮጵያ ላይ በሁሉም አቅጣጫ ተጽእኖ ለማሳደር ነው። »

የሳይበር ጥቃቱ ተፅዕኖ ከመፍጠር በላይ ተጠናክሮ የሚቀጥል ጦርነት ነውና። አስቀድሞ ቅድመ ዝግጅት በማድረጉ የመረጃ መረብ ጥቃቱ ኢላማ በነበሩት ተቋማት ላይ ጉዳት አልደረሰም። ጥቃቱን ማክሸፍ ባይቻል ኖሮ በሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ፤ ፖለቲካዊ እና ሥነ ልቦናዊ ጉዳት ሊያስከትል ይችል እንደነበር ኤጀንሲው መግለጹ የሳይበር ጥቃቱን አደገኝነት አጉልቶ ያሳያል።

ቀጣዩ አውደ ውጊያ በሳይበር ግንባር ስለሆነ የጦር ዕቃውን ታጥቀን ፣ የራስ ቁሩን ደፍተን ፣ ጡሩሩን ለብሰን፣ ጦሩን እየሰበቅ፣ ዘገሩን እየነቀነቀን 24/7 ተጠንቅቀን ልንጠብቅ ይገባል። ከዚህ በኋላ የማይቀርልን ዕዳ/ ዘ ኒው ኖርማል / ነውና። ሰሞነኛው የአገልግሎቱ መግለጫ ይሄንኑ የሚያረጋግጥ ሆኖ አግኝቸዋለሁ።

ለመሆኑ የመረጃ መረብ ወይም የሳይበር ጥቃት ሲባል ምን ማለት ነው? በሰለሞን ሙሉጌታ ካሳ «ግርምተ ሳይቴክ» መፅሐፍ ፤ «የማይታየው ጦርነት» በሚል ምዕራፍ ስር ገፅ 157 ላይ ፤ «... ምስጢራዊ የሆነና ያልሆነን ዲጂታል መረጃን ከባለቤቱ ፈቃድ ውጭ መስረቅ ፣ ይዘቱን ማበላሸት ፣ ከእነ አካቴው ማጥፋት...» ሲል ይበይንና ታሪካዊ ዳራውን እንዲህ ያብራራል።

«ከሙከራ ላብራቶሪ በዘለለ መልኩ የመጀመሪያው ' ኤልክ ክሎነር ' የተባለ የግል ኮምፒውተርን የሚያጠቃ ቫይረስ በ1982 ዓ.ም የ15 አመት ወጣትና የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ በነበረው አሜሪካዊው ሪቻርድ ስክሬንታ ከተፈጠረ ጊዜ ጀምሮ በኮምፒውተር መረጃዎች ያነጣጠረ ' ሳይበር ' ጥቃት በመንግሥታት መካከል ጭምር ሳይቀር የሚካሄድ የሳይበር ጦርነት / ሳይበር ዋር / አሀዱ ብሎ ጀመረ።

በወቅቱ ኢንተርኔት ገና ለሕዝብ ጥቅም ያልዋለበት ጊዜ ስለነበር ወንጀሉ በስፋት አልተስተዋለም። በ1980ዎቹና 90ዎቹ አጋማሽ ድረስ ጥቃቱ በብዛት ይሰነዘር የነበረው እንደ ' ፍሎፒ ዲስክ ' እና ' ሲዲ ' በመሳሰሉ ተንቀሳቃሽ የመረጃ ማስቀመጫ ቁሶች አማካኝነት ቫይረስ ከአንድ ኮምፒውተር ወደ ሌላ ኮምፒውተር በማስተላለፍ ነበር።

በ1990ዎቹ አጋማሽ በኋላ የኢንተርኔት አጠቃቀም እያደገ ሲመጣ ጥቃቱም መልኩን ቀይሮ ብቅ አለ። በ2003 ዓ.ም ገደማ የሳይበር ወንጀል ፍፁም አዲስ በሆነ መልኩ ድረ ገጾችን የማጥቃት አላማ ይዞ ተነሳ። ይህ የሆነበት ምክንያት በወቅቱ የኢንተርኔት ' ኢኮሜርስ ' ግብይት ሥርዓቱ እየተጧጧፈ በመምጣቱ ነው።

በተለይ የክሬዲት ካርድ ቁጥሮችን በመስረቅ ላይ ያነጣጠረ የሳይበር ወንጀል በ2000ዎቹ ተጧጡፎ ቀጠለ። ከ2005 እስከ 2007 ዓ.ም ባለው ጊዜ አልበርት ጎንዛሌዝ የተባለ አደገኛ አሜሪካዊ የኮምፒውተር ሀከርና የሳይበር ወንጀለኛ የተለያዩ ግዙፍ የንግድ ኩባንያዎችን የኮምፒውተር ሲስተሞችን በማጥቃት፤ የግለሰቦችን ክሬዲት ካርዶችን ቁጥር በመመንተፍ 45 ነጥብ 7 ሚሊዮን ዶላር ዘርፏል ። ..." ዛሬ የሳይበር ጥቃት ምርጫን ፣ ኢኮኖሚንና ማኅበራዊ ግልጋሎትን በማስተጓጎል ውድ ዋጋ እያስከፈለ ይገኛል።

ከፍ ብዬ የጠቀስሁት ደራሲና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ባለሙያ በመጽሐፉ ይበልጥ እንዲህ ያብራራዋል። «... የመረጃ ፍሰቱ ዓለምን ማጥለቅለቁ ፤ መንግሥታትም አሠራራቸውን በኢንተርኔትና በኮምፒውተር ማድረጋቸው ፤ መሠረተ ልማታቸውን የሚያስተዳድሩት፤ መረጃዎቻቸውን የሚያስቀምጡት፤ አገልግሎት የሚሰጡት እንዲሁም ታላላቅ ወታደራዊና የደህንነት መረጃዎችን በዲጂታል መልክ መያዛቸው ለጥቃት አጋልጧቸዋል። የእንግሊዝ የደህንነት ተቋማት እነ ኤም አይ ፋይፍና ኤም አይ ሲክስ እንዲሁም የአሜሪካው ኤፍ ቢ አይ የሳይበር ጥቃትን ከፍተኛ የጸጥታ ስጋት አድርገው ወስደው መሥራት ከጀመሩ ውሎ አድሯል ። ... »

ወደ ገጽ 12 ዞሯል

ዜና

# በዓላትን በሰላም ለማክበር የተሠራውን ሥራ በመሪዎች ጉባኤና በዓድዋ በዓል መድገም ይገባል

## - ለሰላም ሠራዊት አመራሮችና አባላት ዕውቅና ተሰጠ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- የአደባባይ በዓላት በሰላም እንዲከበሩ በትብብር የተሠራው ሥራ በአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤና በዓድዋ ድል በዓልም መድገም እንደሚገባ የአዲስ አበባ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ ገለጹ፡፡ የአደባባይ በዓላት በሰላም እንዲከበሩ አስተዋጽኦ ላበረከቱ የሰላም ሠራዊት አመራሮችና አባላት ዕውቅና ተሰጥቷል፡፡

በዕውቅና መርሀ-ግብሩ ላይ ከንቲባ አዳነች አቤቤ እንደገለጹት፤ በቅርቡ የተከበሩት የአደባባይ በዓላት በሰላም እንዲጠናቀቁ የሰላም ሠራዊት አባላት ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡

ሰላም የሁለንተናዊ እንቅስቃሴያችን መሠረት ነው ያሉት ከንቲባዋ፤ ሰላምን ማረጋገጥ ለፀጥታ አካላትና አመራሮች ብቻ የሚተው ሥራ አይደለም ሲሉ ተናግረዋል።

ይህን በመገንዘብ የከተማችን ነዋሪዎች ላለፉት ዓመታት በሰላም ሠራዊት በመደራጀት፣ ራሳችሁን ለሰላም ጠንካራ ዘብ በማድረግ፣ ከፀጥታ አካላትና ከፖለቲካ አመራሩ ጋር ተባብራችሁ በመሥራት ላበረከታችሁት አስተዋጽኦ ምስጋና እናቀርባለን ብለዋል፡፡

በቀጣይ ለሚካሄደው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ ለኢትዮጵያ ትልቅ ትርጉም አለው ያሉት ከንቲባዋ፤ ጉባኤው ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ የሰላምና ፀጥታ ሥራውን አጠናክሮ መቀጠል እንደሚገባ አመላክተዋል።

ቀደምት እናት አባቶቻችን ነፃነታቸውን ለማስጠበቅ



ያስመዘገቡት ትልቅ ታሪክ አዲስ አበባን የአፍሪካ መዲና ማድረግ እንደቻለ ተናግረው፤ በርካቶች የአፍሪካ ኅብረት መቀመጫነትን ከኢትዮጵያ ለማስወጣት ጥረት ቢያደርጉም በትብብር በተሠራው የዲፕሎማሲ ሥራ መዲናነቷን ማጽናት ተችሏል ሲሉ አስረድተዋል።

በቅርቡ በሚካሄደው ጉባኤም የሰላም ሠራዊት አባላትን ጨምሮ ሁላችንም የከተማችን አምባሳደሮች በመሆን እንግዶቻችንን ልንቀበል ይገባል ብለዋል፡፡

በቀጣይነትም ኢትዮጵያውያን የነበራቸውን ልዩነት ወደ ጎን ትተው በጋራ በመቆም ድል ያስመዘገቡበትና የጥቁር ሕዝቦች ተምሳሌት የሆነው የዓድዋ በዓል እንደሚከበር አመላክተው፤ የበዓሉን ትልቅነትና ታሪኩን በሚመጥን መልኩ ለማክበር በጋራ መቆም እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል፡፡

በከተማችን ተደራጅተው አካባቢያቸውን የመጠበቅ እና ወንጀልን የመከላከል ሥራ ላከናወኑና አሁንም እየሠሩ ለሚገኙ የሰላም ሠራዊት አባላት እውቅናና ምስጋና በመስጠት አበረታተናቸዋል ሲሉ ተናግረዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ሰላምና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ ኃላፊ ሊዲያ ግርማ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ አዲስ አበባ የአፍሪካ ኅብረት መቀመጫና ሦስተኛው የዲፕሎማሲ ማዕከል ናት፡፡

በመሆኑም ደረጃዋን የሚመጥን ሰላምና የሕግ የበላይነትን ለማስከበር የፀጥታ ተቋማት ዘመናዊ አሠራር ሊጠናከር እንደሚገባ ተናግረው፤ ቢሮው ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በከተማዋ ለመፈጸም የታቀዱ ሕገወጥ ተግባራት እንዳይሳካ ማድረጉን አስታውቀዋል።

በቅርቡ የተከናወኑ ሕዝባዊና ሃይማኖታዊ በዓላትን ያለ ምንም የፀጥታ ችግር ማክበር መቻሉን አስታውሰው፤ ለዚህም የሰላም ሠራዊቱና የከተማዋ ነዋሪ ላበረከቱት አስተዋጽኦ ምስጋና አቅርበዋል፡፡

በመርሀ ግብሩ ላይ የአደባባይ በዓላት በሰላም እንዲከበሩ አስተዋጽኦ ላበረከቱ የሰላም ሠራዊት አመራሮችና አባላት እንዲሁም ተቋማት ዕውቅና ተሰጥቷል፡፡

# “በኢትዮጵያዊ አንድነቱ የፀና፤ ክንደ ብርቱ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

24ኛውን ዙር የአንድነት የመኮንኖች ኮርስ አጠናቃችሁ ለምረቃ ስለበቃችው እንኳን ደስ አላችሁ ያሉት ፊልድ ማርሻሉ፤ መኮንኖቹ ወደ ጀግናው ሀገር መከላከያ ሠራዊት ስትቀላቀሉ የሠራዊታችን ተደማሪ አቅም ትሆናላችሁ ብለዋል።

ሙሉ ለሙሉ ሉዓላዊነት ያላትን ሀገር ለማስጠበቅ አንድነት ወሳኝ ነው ያሉት ፊልድ ማርሻሉ፣ 24ኛው ዙር የአንድነት የመኮንኖች ኮርስ እንደ ስማችሁ አንድነታችሁን አጥብቃችሁ ተልዕኳችሁን በብቃት መወጣት ይጠበቅባችኋል ብለዋል።

የሀገር መከላከያ ሠራዊት አሁንም የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅምና የሕዝቡን ሰላም ለማስጠበቅ ዝግጁ ነው ሲሉ ፊልድ ማርሻሉ ተናግረዋል።

በሠራዊቱ የ117 ዓመታት ታሪክ ውስጥ መኮንኖች ከአርበኞችና ከጀግናው ሠራዊት ጋር ሆነው የውጭ ወራሪና የውስጥ ባንዳን ተከላክለው ሀገርን በማጽናት ረገድ ከፍተኛ ዋጋ ከፍለዋል ያሉት ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ፤ የጣልያን ፋሽሽት ወረራን ቀልብሰው አባረዋል፤ በዓለም አቀፍ ግዳጆች ጭምር አኩሪ ሥራ ሠርተዋል አሁንም የሀገርን ሉዓላዊነትና አንድነት አጠናክረዋል ብለዋል።

ኢትዮጵያ ለባህር በር በቅርብ ርቀት እያለች ተገፍታ መቆየቷን አንስተው፤ በዚህ ምክንያት የደረሰባትን የኢኮኖሚና የፖለቲካ ስብራቶችን ለመቅረፍ በሰላማዊ መንገድ ባህር በር ለማግኘት ስምምነት ማድረጓን አስታውሰዋል።

ስምምነቱ ያስቆጣቸው ለኢትዮጵያ ዕድገት በጎ የማይመኙ ሀገራት የውስጥ ችግሮቻችንን ለማባባስ የቋመጡበትና የቆረጡበት ጊዜ ላይ ነን ሲሉ ተናግረዋል ።

ተመራቂ መኮንኖችም ክንደ ብርቱው ሠራዊት ጋር በመሆን የኢትዮጵያን ዕድገት የማይመኙ አካላትን እኩይ ሃሳብ ለማምከንና የኢትዮጵያን ጥቅም ለማስጠበቅ ዝግጁ መሆን አለባችሁ ብለዋል።

በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ በየትኛውም አቅጣጫ የሚሰነዘሩ ጥቃቶችን ለመመከት ዝግጁ መሆኗን ገልጸው፤ብሔራዊ ጥቅማችንና ሰላማችን ላይ የሚሰነዘሩ ጥቃቶችን ለማምከን ጀግናው መከላከያ ሠራዊት ዝግጁ መሆኑን አስረድተዋል።

ለኢትዮጵያ በጎ የማይመኙ አካላት የውስጥ ችግራችን እንዲባባስ ሙከራ ማድረጋቸውን አመልክተው፤ በጽንፈኝነት የተሰማሩ አካላት ከዚህ እኩይና ሀገራቸውን ከሚያዳክም ተግባር እንዲቆጠቡ አሳስበዋል።

በሁርሶ ኮንቲጀንት ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት የአንድነት ኮርስ የመኮንኖች ምረቃ ሥነ-ሥርዓት ላይ ተመራቂ መኮንኖቹ ወታደራዊ ሰልፍና ትርዒት ለታዳሚዎች አሳይተዋል።

ተመራቂ መኮንኖቹ ስልጠናውን በአግባቡ ተከታትለው ለሕዝብና ለሀገር ሕይወቱን እየሰጠ ያለውን ጀግናው የሀገር መከላከያ ሠራዊት አመራር ለመሆን መብቃታቸው እንዳስደሰታቸው ገልጸዋል ።

በምረቃ ሥነ ሥርዓቱ ላይ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ፤ ከፍተኛ መኮንኖች፣ የውጭ ሀገራት ወታደራዊ አታሼዎችና ሌሎች የክብር እንግዶች ተገኝተዋል።

# “ኢኮኖሚያችን ላይ አደጋ ለደቀኑ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር በሳይበር ታለንት ሰመር ካምፕ ፕሮግራም ለሁለተኛ ጊዜ ያሰለጠናቸውን 120 ታዳጊዎች ትናንት አስመርቋል።

በፕሮግራሙ የተገኙት የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር በለጠ ሞላ (ዶ/ር) እንዳመለከቱት፤ የሳይበር ደህንነት ስጋቶች በሚያሳስብ ፍጥነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተወሳሰቡና እየጨመሩ መጥተዋል።

የደህንነት ስጋቶቹ መሠረተ ልማቶችን፣ ኢኮኖሚንና የአኗኗር ዘይቤን ጭምር አደጋ ላይ ሊጥሉ ስለሚችሉ ከወዲሁ ዝግጅት ማድረግ እንደሚገባ አመላክተዋል።

የሳይበር ደህንነትና ሉዓላዊነታችንን መከላከል፤ የዲጂታል ሀብቶችና መሠረተ ልማቶቻችንን የመጠበቅ አቅም መገንባት ለነገ የማንለው ወሳኝ ጉዳያችን ነው ሲሉም ሚኒስትሩ ተናግረዋል።

የሳይበር ደህንነትን ከምንም በላይ ማረጋገጥ የሚቻለን ደግሞ ብቁ የሳይበር ደህንነት ባለሙያዎችን ማፍራት ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ብቁ የሳይበር ደህንነት ባለሙያ ለማፍራት መደበኛው ትምህርት ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ቢሆንም በፍጥነት እያደገ ከመጣው የሳይበር ገጽታ ጋር እኩል ለመራመድ ተግባራዊ ልምምድ የሚደረግበት ስልጠና አስፈላጊ መሆኑንም ጠቁመዋል።

የሳይበር ደህንነት አስተዳደር የታለንት ልማት ፕሮግራሞች የሰለጠኑ ባለሙያዎችን በማፍራት ተጠቃሽ መሆኑን ያመላከቱት ሚኒስትሩ፤ ይህም እንደሀገር በዘርፉ ጠንካራ የሰው ኃይል ለመገንባት ያለውን ቁርጠኝነት የሚያሳይ መሆኑን አስረድተዋል።

የትምህርትና የስልጠና ተቋማት፣መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣የፋይናንስ ተቋማትና ባለሀብቶች በዘርፉ በትብብር መስራት እንዳለባቸው ጠቁመው፤ የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ከኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ጋር በመተባበር ለዘርፉ እያደረገ ያለው ጥረት በአርዓያነት የሚጠቀስ መሆኑን ተናግረዋል።

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በዘርፉ ያለውን የሰው ኃይል ክፍተት ለመሸፈን ልዩ ፍላጎት ያላቸው ታዳጊ ወጣቶች የሚሰለጥኑበት የቡራዩ ታለንት ማዕከል ገንብቶ ወደ ሥራ ማስገባቱንም ገልጸዋል።

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር አቶ ሰለሞን ሶካ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ተመራቂዎቹ በሳይበር ደህንነት ያለውን የሰው ኃይል ክፍተት ለመሸፈን ይረዳሉ።

ሀገር የትውልዶች ቅብብል ናት ያሉት አቶ ሰለሞን፤ ኢትዮጵያን ቀና የሚያደርጉ ትውልዶችን በመቅረጽ ለሀገራቸው ሳይሰስቱ በንፁህ እጃቸው የሚሰሩ ትውልዶችን ለማፍራት እንሰራለን ብለዋል።

እንደ ሀገር በዚህ ዓመት በስድስት ወር ውስጥ አራት ሺህ 623 የሳይበር ጥቃቶችን መከላከል መቻሉን ጠቁመው፤ በዚህም 10 ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር ማዳን እንደተቻለ አስታውቀዋል።

ከተለያዩ የሀገሪቷ አካባቢዎች ተውጣጥተው በሳይበር ደህንነትና ተያያዥ ዘርፎች ከተመረቁት 120 ታዳጊዎች መካከል 17ቱ ሴቶች መሆናቸው ተገልጿል።

# ግንባታቸው...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ኮርፖሬሽኑ ከዚህ ቀደም በመንግሥት አስተባባሪነት በቦንድ ብድር ያስገነባቸው ቤቶች ላይ ብድር ስላለበት 36 ቢሊዮን ብር ከዕዳው መቀነስ ቢችልም አሁንም 37 ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ብር ያልተከፈለ ዕዳ እንዳለበት አመላክተዋል፡፡

ዕዳው ተቋሙ በመንግሥት አስተባባሪነት የሚገነባቸው ቤቶች በሚፈልገው ፍጥነት ለማስኬድና ቆጥበው ቤት ላልደረሳቸውም ሆነ አዳዲስ የቤት ፍላጎቶችን ለማስተናገድ የሚያስችል የባንክ ብድር አቅርቦት እንዳያገኝ ማገዱን አስረድተዋል።

የፋይናንስ እጥረቱን ለመፍታትና የመንግሥትን ተሳትፎ ለማሳደግ ኮርፖሬሽኑ ባለፉት አራት ወራት የተገነቡ የመኖሪያና የንግድ ቤቶችን ለጨረታ ለማቅረብ መወሰኑን ዋና ዳይሬክተሩ አስታውቀዋል፡፡

ቤቶቹ በኮርፖሬሽኑና በዲዛይን ግንባታ ቢሮ በኩል በመንግሥት በተመደበ ካፒታል የተገነቡ ሲሆን፤ በሽያጩ በሚገኘው ገንዘብ በአጠረ ጊዜ የሚጠናቀቁ የኪራይ ቤቶችን ገንብቶ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ የከተማዋ ነዋሪዎች ለማስተላለፍ እንደሚውል ገልጸዋል፡፡

ኮርፖሬሽኑ ሁሉንም የቤት አቅርቦት አማራጮችን በማቀናጀት የነዋሪዎችን ቤት ችግር ለመፍታት መስራቱን ይቀጥላል ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ የኪራይ ቤቶችን ለመገንባት የሚደረገው ጥረትም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አመላክተዋል፡፡

ኮርፖሬሽኑ ቤቶችን ከመገንባት ጎን ለጎን በርካታ የከተማዋ ነዋሪ የሥራ ዕድል በመፍጠር ፤የኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂ ዕውቀት ሽግግር በማድረግና በከተማ አስተዳደሩ በባለቤትነት የተያዙ የመኖሪያና የንግድ ቤቶችን የማስተላለፍና የማስተዳደር ሥራ እየሰራ ይገኛል ብለዋል።

የሦስት ሺ 452ቱን ቤቶች የጨረታ ሰነድ ከጥር 27 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ መግዛትና መወዳደር እንደሚቻል ኮርፖሬሽኑ አስታውቋል።

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

## ግብ ግብ ከእሳት ጋር

እፀገነት አክሊሉ

አደጋ በየትኛውም ቦታና ጊዜ እንዲሁም በማንኛውም ሰው ላይ ሳያማክር በዚህ ቀን እደርሳለሁ ብሎ ሳያሳውቅ ድንገት የሚከሰት በመሆኑ ጥሎት የሚያልፈውም ጠባሳ እጅግ ከባድ ነው። እነዚህ አደጋዎች ደግሞ የከፋ ጉዳት ሳያደርሱ መከላከል መቻል ደግሞ ከግለሰብ አልፎ ተቋማትን ጭምር የሚመለከት ነው።

ከእነዚህ ተቋማት መካከል የአዲስ አበባ ከተማ እሳትና አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን አንዱ ነው። ኮሚሽኑ የሰውን ልጆች ሕይወት ከአደጋ ለመከላከል የሀገርና የሕዝብ ሀብትን ከውድመት ለማዳንም ብቁና ምስጉን በሆኑ ባለሙያዎቹ አማካይነት ሃያ አራት ሰዓት ሰባቱንም ቀናት በዓልን ሳይመርጥ ሁሌም አገልግሎት ላይ ያለ ተቋም ነው።

እኛም ለዛሬ የሕይወት ገጽታ አምዳችን በዚሁ ተቋም ለበርካታ አመታት የአደጋ መከላከል ሥራን በውጤታማነት በማከናወን ላይ ስላለችው ወይዘሮ ትዕግሰት ተክለዓብ የሕይወት ተሞክሮ ይዘን ቀርበናል። በአሁኑ ወቅት ትዕግስት በአዲስ አበባ ከተማ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን የአደጋ ምላሽ ቡድን መሪ ናት።

ወይዘሮ ትዕግስት ተወልዳ ያደገችው አዲስ አበባ ከተማ ልዩ ስሙ ቾሎት መድኃኔዓለም በሚባለው ሰፈር ሲሆን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቷንም የተማረችው በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ነው።

«.....ተወልጄ ያደኩበት ቾሎት መድኃኔዓለም ወይም ቀጨኔ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ነው። ለቤተሰቦቼ ሦስተኛ ልጅ ነኝ። እናትና አባቴ ከአካባቢው ልጆች እንዲሁም ከእህትና ወንድሞቼ ጋር በመሆን የአንደኛ ደረጃ ትምህርቴን እማር ዘንድ የላኩኝ ወደ ዳግማዊ ምኒልክ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው። በዚያም ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ያለውን ትምህርት አጠናቅቄያለሁ» ትላለች።

የአንደኛ ደረጃ ትምህርቷን አጠናቃ ሚኒስትሪ ፈተናዋን ተፈትና ጥሩ ውጤት በማምጣት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ለመማር ያቀናቸው ወደ እቴጌ መነን ትምህርት ቤት ነው። በትምህርት ቤቱም አስረኛ ክፍል ይሰጥ የነበረውን የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ወሰደች። ከዚያ በኋላ ግን በትምህርቷ እንዳትቀጥል የሚያደርጋት አጋጣሚ ተፈጠረ።

«......ትምህርት በጣም እወድ ነበር። የሚኒስትሪ ውጤቴም በጣም አሪፍ ነው። በትምህርት ቤት መምህራን የሚያስተምሩትን ነገር በቀላሉ የመረዳት ችሎታ ነበረኝ። ብቻ በጠቅላላው ለትምህርት የነበረኝ ፍቅር በቀላሉ የሚገለጽ አይደለም» በማለት የተማሪነት ጊዜዋን ታስታውሳለች።

ትዕግስት የልጅነት ገጽታዋ (መልኳ ) የሚያምር ሳቢ ስለነበረ ትምህርት ቤት ደርሳ እስክትመለስ ድረስ በየመንገዱ የሚገጥሟት ጾታዊ ትንኮሳዎች አለፍ ሲልም የጓደኝነት ጥያቄው በጣም አስቸጋሪ ሆኑባት፤ ይህ ሁኔታ ደግሞ እሷን ከማሳሰቡም አልፎ ለቤተሰቦቿ ትልቅ ጭንቀት ነበር፤ ልጃችን ትሰናከልብን ይሆን የሚለውም ስጋታቸው ከፍ ያለ ሆኖ ቆይቷል። በዚህ የተነሳ ዘወትር ለሚጠብቃትና ለሚከታተላት አንድ ወጣት ተዳረች። በትዳሯ ደስተኛ ብትሆንም በልጅነቷ በማግባቷ እንደ እኩዮቿ እንደ ልቧ መዝናናት እንዳልቻለች ትናገራለች፡፡

«......ልጅነቴን ተዝናንቼ ተጫውቼ የማሳለፍ ዕድልን አላገኘሁም፤ ከትዳር በፊት በጓደኝነት ያሉ መዝናናቶችም እኔ ጋር አልነበሩም፤ መዝናናት ይሉትን የወጣትነት ክፍል ሳላውቀው አልፌዋለሁ። በዚህም ከትምህርት ወደ ሕይወት□ ከሕይወት ወደመተዳደሪያ ሥራ ነው ያመራሁት » ትላለች።

ትዕግስት ትዳር ወይንም ደግሞ ልጅ ወልዶ ማሳደግ ከምትወደው ትምህርት ማስቆም እንደሌለበት ወሰነች። ልጇን ወልዳ ለታላላቅ እህቶቿ እንዲሁም ለእናቷ በመስጠት በአስረኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ያቋረጠችው ትምህርት ለመቀጠል ወደ ትምህርት ቤት ሄደች።

«......በወቅቱ ልጅ ሆኜ ልጅ አቅፌ መታየት ያስከፋኝ ነበር፤ እናቴና እህቶቼ እንዲይዙልኝ ነበር የማደርገው። ትምህርት ቤት ለመሄድ ደግሞ እሷን ማጥባት ካለቀሰች መቅረት ብዙ ነገሮች ነበሩ ትምህርት ቤት ቁጭ ብዬ ጡቴ ይወጠራል ይህንን ያዩ ጓደኞቼ ደግሞ እንዴ ወልደሽ ነው? አግብተሽ ? የሚሉ ጥያቄዎችን አዘውትረው ይጠይቁኝ ነበር። በጥያቄዎቹ ብከፋም በተቻለ መጠን ራሴን ተቆጣጥሬ ነው የተማርኩት፤» በማለት ሁኔታውን ትገልጻለች።

ባለቤቷ ከሷ በዕድሜም በአቅምም የሚሻል ነበርና ይህንን የልጅነት ድካሟን በጣም እንደሚረዳት ትናገራለች ። ልጅነቷን ተረድቶ በተቻለ መጠን ከሃሳብና ከብስጭት የምትርቀበትን መንገድ በማመቻቸት ቤተሰቧን የምትረዳበትን መንገድ ያመቻችላት ነበር። ራሱን በትምህርት አሻሽሎ የተሻለ ሥራን በመሥራት እሷም በትምህርት ዝቅ እንዳትልበት ልጅ እየያዘላት ትምህርት ቤት እንድትሄድ እንድታጠና ሁኔታዎችን በማመቻቸት የተወጣው ሚና ላቅ ያለ ስለመሆኑና ለዛሬ እዚህ መድረሷም ምክንያቱ እሱ መሆኑን ትናገራለች።

የአራስነት ጊዜዋን ጨርሳ ወደተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ትምህርት ቤት በመግባት በኮምፒዩተር ሳይንስ የዲፕሎማ ትምህርቷን ጀመረች። በዚህም ከአይቲ ድጋፍ ሰጪነት እስከ ጥገና ድረስ ያሉትን ትምህርቶች ተምራም ዲፕሎማዋን አግኝታለች።

ትዕግስት የዲፕሎማ ትምህርቷን ከተማረች በኋላ ሁለተኛ ልጇን ነፍሰጡር ሆነች። ከመጀመሪያው በተሻለ ሥነ ልቦናና አቅም የሁለተኛ ልጇን የእርግዝና ጊዜ በተሳካ ሁኔታ በማጠናቀቅና በሰላም በመገላገል አራስ ቤት ተኛች። በዚህ ጊዜ ግን ታስብ የነበረው ከአራስ ቤት ወጥታ የምትማረውን ትምህርት ነበርና ልክ አራስ ቤቷን አጠናቃ እንደወጣች በቀጥታ የሰው ሀብት አስተዳደር ትምህርት ለመማር ወደ ኮሌጅ ገባች።

የኮሌጅ ትምህርቷንም በተገቢው ሁኔታ አጠናቃ በዲፕሎማ ተመረቀች። ይህም ቢሆን ግን እርካታ ላይ አልደረሰችምና የማኔጅመንት ትምህርቷን በዲግሪ ደረጃ ለማሳደግ ወደ ትምህርት ቤት ሄደች ይህንንም ትምህርት እየተማረች የመጨረሻ ልጇን አርግዛ ስለመውለዷም ነው የምትናገረው።

«......በሕይወቴ ብዙ ብፈተንም በዕድሜዬ ግን ምንም ያባከንኩት ጊዜ ባለመኖሩ ደስተኛ ነኝ፤ ልጆቼን እያሳደኩ ቤቴን እየመራሁ ትምህርቴን እየተማርኩ ሥራዬ ላይም ሳልጎድል እዚህ ደርሻለሁ፤ በዚህም በጣም ደስተኛ ከመሆኔም በላይ አልችልም የሚል አስተሳሰብን ከአእምሮ ማውጣት ብቻ ለስኬት ትልቅ መንገድ መሆኑንም ተረድቻለሁ» በማለት ትናገራለች።

ትዕግስት አሁን ያለችበትን ሥራ ከመጀመሯ በፊት ንግድ እንዲሁም በተለያዩ ቦታዎች ላይ ተቀጥራም ለመሥራት ሞክራለች። የሕይወት አጋጣሚ ብዙ ነውና እሷ ተቀጥራ በሥራ ላይ እያለች እህቷ ፒያሳ የአዲስ አበባ አደጋ ስጋት ኮሚሽን የሥራ ማስታወቂያ አውጥቶ ትመለከታለች። ይህም ሊያመልጠን አይገባም ብላ እራሷንም እህቷንም እንዳስመዘገበቻት ትናገራለች።

«.....በወቅቱ እኔ አራት ኪሎ አካባቢ ወርቅ ቤት ተቀጥሬ እሠራ ነበር፤ እህቴ ደግሞ እንደ አጋጣሚ ማስታወቂያውን ስታይ እኔንም እሷን አስመዘገበች፤ የትምህርት ማስረጃችሁን አቅርቡ በተባለበት ቀን ደግሞ አብረን ሄድን፤ የዛሬ 16 ዓመት የነበረው የመጀመሪያው ቅጥር የሚጠይቀው መስፈርት 8ተኛ ክፍልን ያጠናቀቀ የሚል ነበር። ያም ቢሆን ግን ለማበላለጫ የተጠቀሙት ውጤታችንን ሆነና የእኔ ውጤት አሳለፈኝ እህቴ ሳይሳካላት ቀረ » በማለት ሁኔታውን ታስታውሳለች።

የሥራ መደቡ ጥበቃ በመሆኑም ሥልጠና መውሰድ ያስፈልግ ስለነበር ሥልጠናውን ለመውሰድ ወደሚፈለገው ቦታ በመሄድ ሥልጠናውን በጥሩ ሁኔታ በማጠናቀቅ ወደ ሥራው ስለመግባቷም ነው የምትናገረው።

«.......በወቅቱ ለጥበቃ ሥራ ነው የተመዘገብኩት ስል ብዙ ሰዎች ካለማመናቸውም በላይ እንዴት የሚል ጥያቄ ይመላለስባቸው ነበር። ነገር ግን እኔ በሁኔታው በጣም ደስተኛ ነበርኩ። ደስተኛ የሆንኩበት ዋናው ምክንያት ደግሞ ሥራ በጣም ያስፈልገኝ ስለነበር እንዲሁም ቤት በመቀመጤ የማገኘው ነገር ባለመኖሩ ነው። ውጭ ከሰው ጋር ብውል



ነቃ ብዬ ብዙ ነገሮችን የማሰብ አጋጣሚው ይኖረኛል፤ እለወጣለሁ የሚል የጸና አቋም ስለነበረኝ በጣም ደስተኛ ሆኜ ነው ሥራውን የተቀላቀልኩት» ትላለች።

ትዕግስት በሥራዋ ትጉህ ከመሆኗም በላይ በፍላጎት ትሠራ ስለነበር በቶሎ ነበር ከጥበቃ ሥራ ወደሌላ ክፍል ለመዘዋወር ዕድሉን ያገኘችው። በዚህም ለኦፊሰርነት የወጣውን ውድድር ተወዳድራና በብቃት አልፋ የአደጋ መቆጣጠር ባለሙያ በመሆን ሥራዋን ቀጠለች።

**የአራስነት ጊዜዋን ጨርሳ ወደተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ትምህርት ቤት በመግባት በኮምፒዩተር ሳይንስ የዲፕሎማ ትምህርቷን ጀመረች። በዚህም ከአይቲ ድጋፍ ሰጪነት እስከ ጥገና ድረስ ያሉትን ትምህርቶች ተምራም ዲፕሎማዋን አግኝታለች**

### የአደጋ መቆጣጠር ሥልጠና

«.......ከልጅነቴ ጀምሮ በከባባድ ፈተናዎች ውስጥ ስላለፍኩኝ ሥልጠናውን ተቋቋምኩት እንጂ ሥልጠናውስ ገና ሲገባበት የሚያስፈራ እንዴ እንደዚህ ነው እንዴ? የሚያስብል ነበር፤ ሥልጠናው በእሳት ላይ መዝለል□ ቱቦ ለቱቦ ሄዶ ሰው ማዳን□ እሳት ውስጥ እየዘለሉ ገብቶ ማለፍ□ እንደ ወታደር የአካል ብቃት እንቅስቃሴ መሥራት እና ሌሎች አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ጭምር ማለፍ ይጠይቅ ነበር። ከሁሉም ከባዱ ደግሞ አመጋገቡ ወታደራዊ መሆኑ ነው። የላመ የጣመ ምግብ ብሎ ነገር የማይታሰብ ነበር» ትላለች።

እነዚህንና ሌሎች በርካታ ፈተናዎችን በብቃት መወጣትን የሚጠይቀውን ሥልጠና ትዕግስት ከፍ ባለ ብቃት ከማጠናቀቋም በላይ ሥልጠናውን በዚህ መልኩ መውሰዷ በጥንካሬ ላይ ጥንካሬን እንድትጨምር እንደረዳትም ትገልጻለች።

ለስድስት ወራት ቤተሰብ ምናልባት በሳምንት አልያም በ15 ቀን አንዴ እየታየ ከሚሠለጠንበት የሥልጠና ማዕከል ውስጥ በመቆየትም ሰዎችን ከገቡበት

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

## ግብ ግብ...

ከ6ኛ ገጽ የዞረ

ችግር እንዴት ማዳን ይቻላል የሚለውን ብቻ ሳይሆን ከራስ ጀምሮ ቤተሰበን ብሎም የሥራ ባልደረቦችን እንዴት መምራትና ማስተዳደር እንደሚቻል እውቀት ገብይታበታለች። በሥራ ላይ ብቁና ተፈላጊ ለመሆን ምን ማድረግ ይገባል የሚሉና ሌሎች የሕይወትና የሥራ ክፍሎች ማዳበሪያ ሥልጠናዎችን ማግኘቷንም ነው የምትናገረው።

«......እኔ ሁሌም በሕይወቴ በሥራዬ በእንቅስቃሴዬ ሁሉ መሸነፍ ይሉት ነገር አልፈልግም፤ ከስህተቴ እማር ይሆናል እንጂ አልችልም ብዬ ለመተው አልቸኩልም፤ በዚህ አቋሜም ያንን ከባድ ጊዜ በድል ለማጠናቀቅ በቅቻለሁ። በነገራችን ላይ ከእኔ ጥንካሬና አልሸነፍ ባይነት ጎን ለጎን የባለቤቴ ቀና ትብብርና ድጋፍ ለውጤቴ ማማር ከፍ ያለ ድርሻውን የሚወስድ ነው» በማለት ታብራራለች።

**የመጀመሪያ የአደጋ መከላከል ሥራ**

ማንኛውም ሰው በሠለጠነበት ሙያ ግዳጁን ይወጣ ዘንድ ግድ ነውና ትዕግስትም የሠለጠነችውን አደጋን የመከላከል ትምህርት በተግባር የምትቀይርበት ጊዜ ደረሰ በዚህም «ሀ» ብላ ሥራዋን ትጀምር ዘንድ ቀኑ ደረሰ። እሷም የጓጓችለት ቀን ነበርና ስምሪቱ ሲመጣ ከመቅጽበት ነው ተነስታ የሄደችው።

«.....ከሥልጠና በኋላ ከባባድ አደጋዎች ነበር የገጠሙኝ፤ ለመጀመሪያ ጊዜ ሥራ ተብዬ የተመደብኩትም እህል በረንዳ ተቃጥሎ እሱን ማጥፋት ላይ ነበር። ስደርስም ከሠለጠንኩበት እሳት የባሰ ነበር። በጣም ደነገጥኩ። እንዴት ነው የማጠፋው? ብዬ እራሴን ጠየቅኩ። ከእሳቱ ጋር ግብ ግብ ገጠምኩ። በመጨረሻም አሸነፍኩት። 40 ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሲጠፋ ሳይ እንዴ ለካ እንደዚህ ነው በማለት በራሴ አመኔታን አዳበርኩ» በማለት ትናገራለች።

ልክ እሳቱ መጥፋቱን ወይም በቁጥጥር ስር መዋሉን ስታይ ግን ለካ እንደዚህ ነው ሥራው በማለት ወደውስጧ ማስገባቷን ትነጋራለች። በጣም በሚገርም ሁኔታ እሷን ጓደኞቿ ሥልጠናቸውን አጠናቀው ወደሥራ በገቡበት ጊዜ አንድን ሥራ ሠርተው ልብሳቸው እንኳን ሳይደርቅ ሌላ ጥሪ ይመጣ እንደነበር በማስታወስ የአውቶቡስ ተራውን ሥራ እንዳጠናቀቀች ወዲያው መርካቶ ደግሞ ተመሳሳይ ችግር ተፈጥሮ በመጠራታቸው እሷና ጓደኞቿ ጉዟቸውን ወደዚያ ስለማድረጋቸው ታብራራለች።

«......እንደዚህ ዓይነት ፈጣን ፈጣን አደጋዎችን መሥራት ስጀምር በቃ አደጋ በሁላችንም እጅ ያለ በመሆኑ ማጥፋት እንኳን ባንችል መቀነስ የምንችልባቸው ዕድሎች ስላሉን እሱም ላይ መሥራት አለብኝ በማለት በሩቁ ታየው የነበረውን አደጋ ጠንቅቃ በማወቅ መንስኤና መፍትሔውን በመረዳት ለሌሎች የግንዛቤ ምንጭ በመሆንም መሥራት መቀጠሏን ነው የምታብራራው።

የአደጋ መከላከል ሥራ የወንድ ብቻ የሚመስላቸው ሰዎች ብዙ ናቸው። ነገር ግን ሴትም ትሁን ወንድ ብቻቸውን ሊወጡት የሚችሉት ኃላፊነት አይደለም። በመሆኑ ሁለቱም በሙያው እስከሠለጠኑ ድረስ ያንቺ ያንተ ሳይባባሉ ተጋግዘው ነው መሥራት ያለባቸው፤ እኔም እስከ አሁን ያለፍኩት በዚህ መንገድ ነው።

እኔ የማውቀውን ለወንዱ የሥራ ባልደረባዬ እነግረዋለሁ እንዲህ ብታደርገው ውጤቱ ይህ ይሆንልሃል ብዬ መንገድ እጠቁመዋለሁ። እነሱም ለእኔ እንደዚያው ናቸው ይህንን አድርጊው በዚህ በኩል ሁኚ ብቻ ተጋግዘንና ተባብረን የተቸገረን አካል እየረዳን ነው እዚህ የደረስነው በማለት የእርስ በእርስ መረዳዳቱን ታብራራለች።

«.....እኔ በሕይወቴ አልችልም የምለው ሥራ የለም። እስከ አሁን የገጠሙኝ የሥራ ጓደኞቼም የሚያበረታቱ መንገድ የሚያሳዩ ለችግሮቼ መፍትሔ የሚፈልጉ ብዙ የተማርኩባቸው ናቸው፤ አሁን ለደረስኩበት ደረጃም ትልቁን ምስጋና የሚወስዱት ተቋሙና የሥራ ባልደረቦቼ ናቸው» ትላለች።

የተቋሙ ሥራ በማንኛውም ጊዜና ቦታ የሚሠራ ከመሆኑ አንጻር በተለይም በዓላት እንደ ትዕግስት ላሉ የቤተሰብ ኃላፊዎች ፈታኝ ነው። ምን ጊዜም የበዓላት ቀናት በተጠንቀቅ ስለሚሆኑ በዓልን በቤታቸው ከቤተሰቦቻቸው ጋር ተሰብስበው የማክበሩ ዕድልም በጣም የመነመነ ነው፡፡

ትዕግስት በዓልን አላውቀም ልጆቼም እኔን በዓል አይተውኝ አያውቁም ትላለች።

«......መጀመሪያ ላይ በተለይ በዓል ሲሆን ለእኔም ሆነ ለቤተሰቤ ሁኔታው በጣም ከባድ ነበር፤ የእኔ ጥሩ ዕድል እናቴ በመኖሯ ልጆቼና ባለቤቴ በዓልን እዚያው ሄደው ያሳልፉሉ፤ ይህም ቢሆንም ግን በጣም ከባድ ነው። ምናልባት ዋዜማውን ቤቴ የምሆን ከሆነ ከልጆቼ ጋር ላከብር እችላለሁ። በዓልን ግን በቤት ውስጥ ምን እንደሚመስል የማየት ዕድሉ አይገጥመኝም » በማለት ታብራራለች።

«የከተማዋ ነዋሪ በሰላም በደስታ ያለምንም አደጋ ማሳለፉን ነው ለእኔ በዓሌ» የምትለው ትዕግስት ይህንን ካወቅኩ በኋላ በዓሉ አልፎም ቢሆን እንኳን ዳግም በዓል አስመስዬ ማክበሬም አይቀርም፤ በዚህም ደስተኛ ነኝ ትላለች።

«......በዓል ምናልባትም ደስታ ነውና ካለፈም በኋላ ቢሆን ደስታን ማክበር ቀላል ነው። ነገር ግን ከሁሉም የሚከብደው ኀዘን ሲመጣ ነው። ለምሳሌ አዲስ አበባን በሚያጎራብቷት ክልሎች አካባቢ አደጋዎች ሲከሰቱ የምንጠራው እኛ ነን። እዚያ በሄድንበት ወቅት ደግሞ የቅርብ ሰው ሊያልፍ ይችላል። ምናልባት ቀብር ላይ መድረስ ላንችል እንችላለን ፤ ይህ በጣም የሚከብድ ነው» በማለት ትናገራለች።

**የማይረሱ የሥራ ገጠመኞች**

የአደጋ መልካም የለውም። ሁሉም አደጋዎች አሳርፈው የሚሄዱት የራሳቸው ጠባሳ አላቸው። አንዳንድ ጊዜ አደጋ ከደረሰባቸው ሰዎች አልያም በአደጋ የሚወዱትን ካጡ ሰዎች በላይ የአደጋ መከላከል ሥራውን ሲሠሩ የነበሩ ሰዎችም ልባቸው በኀዘን የሚመታባቸው አጋጣሚዎች ብዙ ናቸው። ትዕግስትም የአደጋ ስጋትን ለመቀነስ በሄደችባቸው ቦታዎች ሁሉ የምታያቸው ነገሮች እጅግ ልብ የሚነኩና የሚያሳዝኑ ቢሆኑም አንዳንዶቹን ደግሞ ለመርሳት ሁሉ እስከመቸገር በራሷ ላይም ጤናዋን እስከ ማዛባት የደረሱ እንደነበሩ ትናገራለች።

«.......አንድ ወቅት መነን አካባቢ እሳት ተነስቶ አንድ ቤት ውስጥ ተቃቅፈው ተኝተው የነበሩ እናትና ልጆች እንደተቃቀፉ በእሳቱ ተቃጥለው በጭሱ ታፍነው ሕይወታቸውን ያጡበት ሁኔታ እስከ አሁንም የማልረሳው በጣም የሚያሳዝነኝ አደጋ ነበር። በተመሳሳይም በበዓል ወቅት ቤተሰብ እየተዝናና በአንድ መኪና ተሞልተው የሚሄዱ ቤተሰቦች ላይ የደረሰው አደጋ አልረሳውም» ትላለች።

ትዕግስት ትቀጥላለች ‹‹አንዳንድ ጊዜ በሕይወት አለመመቻቸት በተለያዩ ምክንያቶች እህቶቼ ጽንስ ይፈጠርባቸዋል። ዘጠኝ ወር ተሰቃይተው ከወለዱ በኋላ በማይሆን ቦታ በሽንት ቤት በወንዝ ዳር ብቻ በጣም በሚዘገንኑ ቦታዎች ላይ ሕፃናትን ይጥላሉ። አንዳንዶች ግን በመጸዳጃ ቤት ፍሳሽ ተጎድተው በአውሬ ተበልተው ስናገኛቸው ልብ ይሰብራል። ›› ትላለች፡፡

በተለይም ላዛሪስት አካባቢ በጎርፍ ተወሰደ ተብሎ እስከአሁንም ድረስ ደብዛው የጠፋውን ሕፃን ልጅ ሌሊቱን ሙሉ ቱቦ ለቱቦ እየዞረች መፈለጓንና ውጤት ማጣቷን ስታስብ በጣም እንደምታዝንም ነው የምትናገረው።

«.....እንደዚህ ዓይነቶቹን አደጋ ሳይ ቤት ያሉትን ልጆቼን ሁሉ በሕይወት የማላገኛቸው ስለሚመስለኝ በጣም እጨነቃለሁ። ይህ ጭንቀቴ ደግሞ አንዳንድ ጊዜ ተባብሶ ወደብቸኝነት፤ ወደመርሳት ችግር እየገፋፋኝ ነው» ትላለች።

**ሥራው ይብቃኝ ብዬ አላውቅም**

«.......ሥራው በጣም ከባድ ነው። እንደነገርኩሽ አንዳንድ አደጋዎች ከውስጥ አይጠፉም፤ ግን ደግሞ እኔ ሥራዬ በደሜ ውስጥ ያለ ከመሆኑ አንጻር አንድም ቀን ይብቃኝ፤ ልተወውና ሌላ ሥራ ልሥራ ብዬ አላውቅም እንዲያውም እረፍት ስሆን ከተማው እንዴት ዋለ? አደጋ የት ነበር? ምን ዓይነት አደጋ ነው የተከሰተው? የሚሉትን ስጠይቅ እና መገናኛ ብዙኃንን ስከታተል ነው የምውለው» በማለት ለሥራዋ ያላትን ፍቅር ትገልጻለች።

**በአደጋ ዙሪያ ቢሠራ የምትለው**

አደጋ አማክሮ የማይመጣ ከመሆኑ አንጻር እንደ ግለሰብም ሆነ እንደ ሀገር ብዙ ግንዛቤን ሊጨምሩ የሚችሉ ተግባራት መሠራት ያለባቸው ይመስለኛል። አንድ ሱቅ ውስጥ ነዳጅ ዘይት፤ ስፖንጅ፤ ሸቀጣሸቀጥ ሁሉም ይሸጣል። ይህ ሱቅ አይበለውና የእሳት አደጋ ቢያጋጥመው ሁሉም ነገሮች ተቀጣጣይ በመሆናቸው የሚደርሰው ጉዳት ከባድ ነው። በመሆኑ ይህንን የሚያደርጉ ሰዎች ግንዛቤያቸው ሊያድግ ከድርጊታቸውም ሊቆጠቡ ይገባል።

በተመሳሳይ ከተማችን ላይ አሁን አሁን ሰማይ ጠቀስ የሚባሉ ሕንፃዎች እየተገነቡ ነው። እነዚህ ሕንፃዎች የእሳት አደጋ ቢያጋጥማቸው የሚመጥናቸው ማጥፊያ የለንም። ይህም ሊታሰብበት የሚገባ ጉዳይ ነው። ከሁሉም በላይ ደግሞ እኛ አደጋን የመከላከል ሥራ የምንሠራው ሰዎች ከአልባሳታችን ጀምሮ ዘመናዊ የሆነና ፈጣን ምላሽን ለመስጠት የሚያግዙ መሣሪያዎችን ልንላበስ ያስፈልጋል። ይህ ግን እየሆነ አይደለም። በመሆኑም ምን ጊዜም አደጋ ዛሬ እንጂ ነገ የሚመጣ ባለመሆኑ ተገቢው ትኩረት ሊሰጥ ይገባል ትላለች።

«...... ከተማችን አድጋለች፤ ግንባታዎች ጨምረዋል። ከተማዋ ሰፍታለች፤ ነገር ግን ለዘርፉ የተሰጠው ትኩረት አናሳ ነው። ካቶ ክሬንና ሄሊኮፕተር እንኳን ይገዛል ከተባለ ዓመታት ተቆጥረዋል። በመሆኑም እንደ ሌላው ዓለም በዘመናዊ መሣሪያ የተደራጀ ተቋም ማፍራት ቢከብደን መሠረታዊ ነገሮች የተሟሉለት ብሎም በተመሳሳይ ሰዓት ተመሳሳይ አደጋዎች ቢከሰቱ ምላሽ ለመስጠት የማይቸገር ተቋም መመስረት ይገባናል። ኅብረተሰቡም የእሳት አደጋ መኪና እየጮኸ ሲመጣ ከመከተል ይልቅ ቅድሚያ ለመስጠት ቢሞክር» በማለት መልዕክቷን ታስተላልፋለች።

**አሁናዊ ሁኔታ**

ትዕግስት አሁን ላይ የአደጋ ምላሽ ቡድን መሪ ናት። የምትወደውን ሥራ በጥሩ ሁኔታ እየሠራች ቤተሰቧን እየመራችና የአራተኛ ዓመት የዲግሪ ትምህርቷን እየተከታተለች ትገኛለች።



**ላዛሪስት አካባቢ በጎርፍ ተወሰደ ተብሎ እስከአሁንም ድረስ ደብዛው የጠፋውን ሕፃን ልጅ ሌሊቱን ሙሉ ቱቦ ለቱቦ እየዞረች መፈለጓንና ውጤት ማጣቷን ስታስብ በጣም እንደምታዝንም ነው የምትናገረው**

# «ማይስ ቱሪዝም»-

## የኅብረቱን ጉባኤ እንደ ማነቃቂያ

ዳግም ከበደ

37ኛው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ በመጪው የካቲት ወር መጀመሪያ በመዲናችን አዲስ አበባ ይካሄዳል። የአህጉሪቱ መሪዎች፣ ሚኒስትሮች፣ ዲፕሎማቶች እና በርካታ የዓለም አቀፍ ተቋማት ድርጅቶች ኃላፊዎችና ሌሎች ተፅእኖ ፈጣሪ ሰዎች በዚህ ስብሰባ ለመሳተፍ ወደ ኅብረቱ መቀመጫ አዲስ አበባ ይመጣሉ።

ኅብረቱ ይህን ጉባኤ ለማስተናገድ ዝግጅቶች መደረጋቸውን አስታውቋል። ኢትዮጵያም በተመሳሳይ ብሔራዊ ኮሚቴዎችን በማቋቋም ጉባኤው በስኬት እንዲጠናቀቅ በጸጥታና ደህንነት፣ በመስተንግዶ በኩል በትኩረት እየተሠራ መሆኑን ይፋ አድርጋለች።

ይህ ጉባኤ የልዩ ልዩ ዓለም አቀፍ ተቋማትና ዲፕሎማቶች መቀመጫም ለሆነችው ኢትዮጵያ በተለይ ለአዲስ አበባ ከተማ ያለው ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ከፍተኛ እንደሆነ ይታወቃል። እንዳለፉት በርካታ አመታት ሁሉ የሀገሪቱንና የዋና ከተማዋን አዲስ አበባን መልካም ገፅታ መገንባትም ይችላል።

አህጉር አቀፍና ዓለም አቀፍ ትኩረትን በከፍተኛ ደረጃ የሚስቡ እንደ አፍሪካ ኅብረት ያሉ ስብሰባዎች በተለይ ለሁነት (ማይስ) ቱሪዝም እድገት የጎላ ፋይዳ ያላቸው ስለመሆኑ የዘርፉ ምሁራንም ያመለክታሉ። በእነዚህ መድረኮች የሚገኙ ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃን፣ ዲፕሎማቶች እና ሌሎች ባለድርሻዎች የኢትዮጵያን የቱሪዝም ሀብት እንዲያውቁና እንዲያስተዋውቁ ዕድሉን ከመፍጠሩ በላይ የሆስፒታሊቲው ዘርፍ እንዲያድግና የሚያስገኘው ኢኮኖሚያዊ ጥቅምም እንዲጨምር እንደሚያስችል የቱሪዝም ዘርፉ የተለያዩ ተቋማት ኃላፊዎች ይጠቁማሉ።

የቱሪዝም ሚኒስቴር የስትራቴጂክ ዩኒት አስተባባሪ አቶ ቴዎድሮስ ደርበው እንደሚሉት፤ ሀገሪቱ ካሏት የታሪክ ትሩፋቶች መካከል አንዱ አዲስ አበባ ከተማ የአፍሪካ ኅብረትና ሌሎች ዓለም አቀፍ ድርጅቶች መቀመጫ መሆኗ ነው። ይህም የሁነት ቱሪዝምን ለማስፋፋት እንደ ሀገር ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር እያስቻለ ነው።

በዚህ ረገድም 37ኛውን የኅብረቱን ጉባኤ ለማስተናገድ እንዲሁም ከጉባኤው በቱሪዝም ዘርፍ ተጠቃሚ ለመሆን በርካታ እንቅስቃሴዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ። በተለይም ሀገርን፤ ያሉትን የቱሪዝም ጸጋዎች፤ የቱሪዝም ምርትና አገልግሎቶችን የማስተዋወቅ ሥራዎችን ለመሥራት ዝግጅት እየተደረገ ነው። ሀገሪቱ ለቱሪዝም ልማት፣ ለጉብኝት እና መሰል እንቅስቃሴዎች ያላትን ምቹነት ወይም ተመራጭነት የማስተዋወቅ ሥራ መሥራት ይጠበቃል። በመሆኑም ጉባኤውን በመጠቀም የገጽታ ግንባታ ሥራዎች ይከናወናሉ። የሀገሪቱን (ብራንድ) መለያ (ላንድ ኦፍ ኦሪጅን) ምድረ ቀደምትነት በቀዳሚነት ለማስተዋወቅ ይሠራል።

"የአፍሪካ ኅብረት ጉባኤ ተሳታፊዎች በሚኖራቸው ቆይታ ከዋናው አጀንዳቸው ጎን ለጎን ስለ ኢትዮጵያ እንዲያውቁ በአዲስ አበባ እና በአዲስ አበባ ዙሪያ ጉብኝት እንዲያከናውኑ ለመቀስቀስ የሚያስችሉ ሥራዎችን እንሠራለን" የሚሉት አቶ ቴዎድሮስ፤ ይህም የገበያ (የማርኬቲንግ) እና የማስተዋወቅ ሥራዎችን የሚያጠቃልል እንደሆነ ይናገራሉ። የሚከናወነውም በአፍሪካ ኅብረት ቅጥር ግቢ ውስጥና እንግዶች በሚያርፉባቸው ሆቴሎች መሆኑን ጠቁመዋል። በመለያ (ብራንድ) ላይ ግንዛቤ የማስጨበጥ፣ የቱሪዝም ጸጋዎችን የማስተዋወቅ ሥራዎች እንደሚከናወኑ ጠቅሰው፤ ይህም በቅንጅት እንደሚሠራና ሥራውም የቱሪዝም ሚኒስቴር ኃላፊነት መሆኑን ተናግረዋል።

የሁነት(ማይስ) ቱሪዝም ለኢትዮጵያ ቱሪዝም ልማት እጅግ ሰፊ ድርሻ እንዲኖረው ማድረግ ይቻላል የሚሉት አቶ ቴዎድሮስ፤ ይህንንም ለማድረግ ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ ብራንድ ሆቴሎች በአዲስ አበባ ተስፋፍተዋል ይላሉ። በቀጣይም ወደ ሥራ የሚገቡ በርካታ ሆቴሎች እንዳሉ ጠቁመዋል። በሌላም በኩል ከዚህ በፊት የተሠሩት እንዳሉ ሆነው በአሁኑ ወቅትም የተለያዩ የስብሰባ ማዕከላት እየተገነቡ እንደሚገኙ ይናገራሉ።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ የአካባቢውና የቀጣናው መናኸሪያ (ሀብ) እንደሆነ ጠቅሰው፣ አየር መንገዱ ወደ ተለያዩ መዳረሻዎች የሚሄዱ ተጓዦች መተላለፊያ መሆኑንም ገልጸዋል፤ አፍሪካን ከተቀረው ዓለም ጋር በማገናኘት እንደሚታወቅም ጠቁመዋል።

እነዚህን መልካም ሁኔታዎች ግምት ውስጥ በማስገባት መንግሥት የቱሪዝም ዘርፍ ከኢኮኖሚ መስኮች እንደ አንዱ በማድረግ በርካታ ደረጃቸውን የጠበቁ የቱሪስት የመዳረሻ ስፍራዎች እየገነባ እንደሚገኝ ያስረዳሉ። ይህም የሁነት ቱሪዝምን በኢትዮጵያ ለማስፋፋት ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር አመላክተዋል።

የአፍሪካ ኅብረት ጉባኤ ለማይስ ቱሪዝም እና ለሀገር ገፅታ ግንባታ ያለውን ፋይዳ በተመለከተ የዝግጅት ክፍላችን ላነሳላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ እንዳብራሩት፤ ይህ ለ37ኛ ጊዜ በአዲስ አበባ ለሚካሄደው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ ዝግጅት በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስተባባሪነት የሚመለከታቸው አካላት ያቀፈ ብሔራዊ አስተባባሪ ኮሚቴ መዋቀሩን አቶ ቴዎድሮስ ደርበው አስታውቀዋል፤ ከእነዚህም መካከል እንግዶቹ የተሳካ ቆይታ እንዲኖራቸው በማድረግ በኩል የቱሪዝም ሚኒስቴር የራሱን ድርሻ ወስዶ እየሠራ እንደሚገኝ ይገልፃሉ።

አቶ ቴዎድሮስ እንዳሉት፤ በጉባኤው በርካታ ቁጥር ያላቸው የአፍሪካ ሀገራት መሪዎችና የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተወካዮች ተሳታፊ ይሆናሉ ተብሎ ይጠበቃል። እነዚህ እንግዶች የሚስተናገዱባቸው ሆቴሎችና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሀገርን ስም በመልካም ሊያስጠሩና የሀገርን ገጽታ የሚገነባ ጥራት ያለው አገልግሎት እንዲሰጡ አቶ ቴዎድሮስ ጥሪ አቅርበዋል።

የሆቴል አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶችም የእንግዶቹን ደህንነት በተጠበቀ መልኩ በኢትዮጵያዊ ሥነ ምግባር፤ ጨዋነትና እንግዳ አቀባበል ማስተናገድ ይጠበቅባቸዋል የሚሉት የስትራቴጂክ ዩኒት አስተባባሪው፤ ሆቴሎች ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት በመስጠት የጉባኤው ተሳታፊዎች በኢትዮጵያ በሚኖራቸው ቆይታ ጥሩ ትዝታ እንዲኖራቸው የማድረግ ኃላፊነት እንዳለባቸው ያሳስባሉ።

ይህንን ለማሳካትም ተሳታፊዎቹን ያስተናግዳሉ ከተባሉ ባለ ኮከብ ሆቴሎች ሥራ አስኪያጆች ጋር መድረክ ተዘጋጅቶ ውይይት መካሄዱንም ይገልፃሉ። እሳቸው እንዳስታወቁት፤ በውይይቱም እነዚህ ሆቴሎች ለሚከፈላቸው ገንዘብ ተመጣጣኝ ክፍያ እንዲያቀርቡና ያለአግባብ ዋጋ እንዳይጨምሩ፣ እንዲሁም ሆቴሎቹ ከጤናና ከድንገተኛ አደጋ ጋር በተያያዘ አስፈላጊውን ዝግጅት እንዲያደርጉ ከስምምነት ተደርሷል። በቀጣይም በከፍተኛ ኃላፊዎች ደረጃ ሆቴሎቹ በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ዝግጅት እያደረጉ ስለመሆኑ በአካል በመገኘት ጉብኝት ይደረጋል። በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በኩልም ከመብራት፤ ከውሃና ቴሌኮም አገልግሎት ጋር በተያያዘ ችግር የሚገጥም ከሆነ በወቅቱ ለመቅረፍ ክትትልና ድጋፍ ይደረግላቸዋል።

አቶ ይታሰብ ስዩም የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ምክትል ዋና ዳይሬክተር ናቸው። እርሳቸው የሚመሩት ተቋም ከ50 ዓመታት በላይ በሆስፒታሊቲና ቱሪዝም ዘርፍ የሚሠሩ ባለሙያዎችን በማሰልጠን ወደ ኢንዱስትሪው ቀላቅሏል። ባለሙያዎቹ በልዩ ልዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በሚገኙ የቱሪዝም መዳረሻዎች እንዲሁም አገልግሎት ሰጪዎች ውስጥ እየሠሩ ይገኛሉ። የዝግጅት ክፍላችንም በቅርቡ የሚካሄደውን የኅብረቱን ጉባኤ በማስመልከት የኢትዮጵያን ገፅታ እና የቱሪዝም ሀብት ለማስተዋወቅና የማይስ ቱሪዝም ፅንሰ ሃሳብን ለማሳደግ "ይህን አጋጣሚ በምን መልኩ ልንጠቀመው ይገባል?" የሚል ጥያቄ አንስቶላቸዋል።

"የአፍሪካ ሀገራት መሪዎች ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ 'የአፍሪካ መዲና አዲስ አበባ ነች' በሚል እሳቤ ነው" የሚሉት አቶ ይታሰብ፤ መስተንግዶው እንደ አንድ ሆቴል አገልግሎት ሰጥቶና ገንዘብ ተቀብሎ መሸኘት ብቻ አለመሆኑን ይናገራሉ። መስተንግዶው ከገፅታ ግንባታ ጋር ቀጥታ ግንኙነት እንዳለው ጠቅሰው፤ ጉዳዩ በጥንቃቄ መያዝ እንደሚኖርበት ያሳስባሉ።

አቶ ይታሰብ ከሳምንት በፊት እርሳቸው በምክትል ዋና ዳይሬክተርነት የሚመሩት የማሠልጠኛ ኢንስቲትዩት ከአዲስ አበባ ባህል፣ ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ጋር በመተባበር ወደ 80 ለሚደርሱ የተመረጡ ሆቴሎች በሥራ ላይ የማማከር አገልግሎት (consultancy service) መስጠቱን ይገልፃሉ። ይህም ጉባኤው በሚካሄድበት ወቅት እንግዶችን በሚፈለገው የጥራት ደረጃ እንዲቀበሉና እንዲያስተናግዱ ያስችላቸዋል ይላሉ።

ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እንዲሁም የሆስፒታሊቲ ዘርፉ ተዋንያን የአፍሪካ ኅብረት ጉባኤ ሲደርስ ብቻ ሳይሆን ሁሌም ዝግጁ ሆነው መጠበቅ እንዳለባቸው ይመክራሉ። የይድረስ ይድረስ ዝግጅት የኢትዮጵያን የማይስ ቱሪዝም እና የቱሪስት ፍሰቱን እንደማያሳድገው አስገንዝበው፣ ሁልጊዜም ቢሆን ሆቴሎችና የመስህብ ስፍራዎች ለውጥና የማያቋርጥ እድገት ማምጣት እንደሚጠበቅባቸው አስታውቀዋል። የትምህርትና ሌሎች ባለድርሻ አካላትም ድጋፍና ክትትል ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው ገልፀዋል።

አቶ ይታሰብ እንዳሉት፤ የአፍሪካ ኅብረት ጉባኤ ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን የጠበቁ ስብሰባዎችን በማዘጋጀት የማይስ ቱሪዝም ዘርፍ ተጠቃሚ ለመሆን ዕድሉን የሚከፍት ልምድ ለማዳበር ያስችላል። ይሁን እንጂ መሪዎች የሚገኙበት እና በኅብረቱ ጽሕፈት ቤት የሚደረግ ጉባኤ እንደመሆኑ ከደህንነትና ጥበቃ አንፃር ጥበቃ ይደረግለታል። ይህ አጋጣሚ ልክ እንደሌሎቹ ጉባኤዎች ነፃነት የሚሰጥ ባይሆንም ጎን ለጎን በሚካሄዱ ዝግጅቶች መሪዎችን፣ ዲፕሎማቶችን እና ልዑካኑን ስለ ኢትዮጵያ መስህቦች እንዲያውቁ ዕድል መፍጠር ያስፈልጋል። ይህን ማድረግ ከተቻለ የኢትዮጵያን ገፅታ ከመገንባት ባሻገር የቱሪዝም ሀብቶችን ለማስተዋወቅ ያስችላል።

"የማይስ ቱሪዝም ፅንሰ ሃሳብን ለማስረፅ እና ለማሳደግ እንደ ሀገር ብዙ መሥራት ይጠበቅብናል" የሚሉት አቶ ይታሰብ፤ ሚሊኒየም አዳራሽን የሚያክሉ አሊያም ከዚያም የላቀ ግዝፈት ያላቸው አዳራሾች (convention center) በመገንባት፤ ዓለም አቀፍ ስብሰባዎችን፣ ኤክስፖዎችን ወደ ሀገር በማምጣት ከዘርፉ የበለጠ ተጠቃሚ መሆን እንደሚያስፈልግ ይመክራሉ። ለዚህ እንዲረዳ አዲስ አበባ የአፍሪካ መዲናና ታላላቅ ስብሰባዎች (እንደ አፍሪካ ኅብረት ጉባኤ) የሚዘጋጅባት እንደሆነች በስፋት ማስተዋወቅና ከዚያ ዕድል ተጠቃሚ መሆን እንደሚያስፈልግ ያስረዳሉ።

በአፍሪካና በዓለም አቀፍ ደረጃ ትላልቅ ኤክስፖዎች (trade fairs) እንደሚካሄዱ የሚናገሩት አቶ ይታሰብ፤ ይህን መሰል ዝግጅት ለሀገራቱ በርካታ ዕድል ይዞ እንደሚመጣ ይናገራሉ። ምርቶቻቸውን ለማስተዋወቅ ከሚመጡት ጋር የእውቀት ሽግግር ይደረጋል፤ የሥራ ዕድል ይፈጠራል፤ የሆቴል ዘርፉ፣ ግብይቱ፣ በአጠቃላይ ኢኮኖሚው ይነቃቃል፤ የቱሪዝም መስህቦች መነቃቃት ይፈጠራል ሲሉ ያብራራሉ።

ይህንን ዕድል ወደ ኢትዮጵያ ለማምጣት በትኩረት መሥራት እና የመሰናዶ ስፍራዎችን ማዘጋጀት እንደሚገባ የሚናገሩት ምክትል ዳይሬክተሩ፤ ከዚህ አኳያም ጅምር ሥራዎች እዚህም እዚያም እንደሚታዩ ጠቅሰዋል፤ ወጥ በሆነ መንገድ ስኬታማ ለመሆን ግን በርካታ ጥረቶችን በማድረግ ውጤቶች መመዝገብ እንደሚኖርባቸው አስረድተዋል።

ከአፍሪካ ኅብረት ጉባኤ ተጠቃሚ ለመሆን በርካታ ሆቴሎች በጉጉት ይጠብቁታል ያሉት አቶ ይታሰብ፤ ይሁን እንጂ በኅብረቱ ጉባኤ ላይ ብቻ ጥገኛ የሆነ የሆስፒታሊቲ ኢንዱስትሪ መኖር እንደሌለበት ይናገራሉ። ይልቁኑም መሰል ታላላቅ ዝግጅቶች በማይስ ቱሪዝም ዘርፍ እንዲዘጋጁና በየወቅቱ ገበያ እንዲፈጠር፣ የኢትዮጵያ የመስህብ ሀብቶች እንዲተዋወቁ እንዲሁም ኢኮኖሚው እንዲነቃቃ ተከታታይ ሥራ በመንግሥትም ሆነ በግሉ ዘርፍ መሥራት እንዳለበት አስገንዝበዋል።

መረጃዎች እንደሚጠቁሙት፤ ማይስ ቱሪዝም በዓለማችን ላይ ከፍተኛ ገቢን የሚያንቀሳቅስና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ተመራጭ እየሆነ የመጣ የቱሪዝሙ ንዑስ ዘርፍ ነው። ያደጉ ሀገራት ከመስህብ ቱሪዝም በተጨማሪ ምጣኔ ሀብታቸውን በሚደግፈው በእዚህ ግዙፍ ኢንዱስትሪ ላይ ትኩረታቸውን አድርገው እየሠሩ ይገኛሉ።

ማይስ ቱሪዝም በሆቴልና ሆስፒታሊቲ፣ ዓለም አቀፍ ስብሰባ፣ ለማበረታቻና ሽልማት የሚካሄዱ የተቋማት ስብሰባዎች እንዲሁም ወቅትን ጠብቀው የሚካሄዱ የንግድ ኤግዚቢሽን ላይ የሚያተኩር የቱሪዝም ዓይነት ነው።

እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ2017 የተካሄደ ዓለም አቀፍ ጥናት እንደጠቆመው፤ ማይስ ቱሪዝም አንድ ትሪሊዮን የአሜሪካ ዶላር የሚያንቀሳቅስ ግዙፍ የቱሪዝም ኢንዱስትሪ ነው። ይህ አሃዝ እስከ 2025 (ከሁለት ዓመታት በኋላ) ወደ አንድ ነጥብ 5 ትሪሊዮን የአሜሪካ ዶላር እንደሚያደግ ጥናቱ ቅድመ ግምቱን አስቀምጧል። ከዚህ መረዳት የምንችለው የሆቴል፣ ኮንፍረንስ፣ ኤግዚቢሽንና ባዛር እንዲሁም ልዩ ልዩ የማይስ ቱሪዝም ንዑሶችን የሚይዘው ይህ ኢንዱስትሪ የዓለማችን የምጣኔ ሀብት ምንጭ እየሆነ መጥቷል።

**ይህንን ዕድል ወደ ኢትዮጵያ ለማምጣት በትኩረት መሥራት እና የመሰናዶ ስፍራዎችን ማዘጋጀት እንደሚገባ የሚናገሩት ምክትል ዳይሬክተሩ፤ ከዚህ አኳያም ጅምር ሥራዎች እዚህም እዚያም እንደሚታዩ ጠቅሰዋል፤ ወጥ በሆነ መንገድ ስኬታማ ለመሆን ግን በርካታ ጥረቶችን በማድረግ ውጤቶች መመዝገብ እንደሚኖርባቸው አስረድተዋል**

# ሳምንቱን በታሪክ

## የመጀመሪያዋ ሴት ጋዜጠኛ ሮማነወርቅና የነፃነት አባቱ ማህተመ ጋንዲ

**ዋስልኝ አየለ**

የጠቅላላ ዕውቀት ጥያቄና መልስ ውድድሮች ላይ ‹‹በኢትዮጵያ የመጀመሪያዋ ሴት ጋዜጠኛ ማን ናት?›› ተብሎ ሲጠየቅ እንሰማለን። የሴቶችን ተሳትፎ ታሪክ በሚዘክሩ መድረኮችና የመገናኛ ብዙኃን አውታሮች ስሟ ይነሳል። በኢትዮጵያ የመጀመሪያዋ ሴት ጋዜጠኛ ሮማነወርቅ ካሳሁን። በዛሬው ሳምንቱን በታሪክ ዓምዳችን 52 ዓመታትን ወደ ኋላ መለስ ብለን በዚህ ሳምንት ጥር 23 ቀን 1964 ዓ.ም ሕይወቷ ያለፈውን፣ ጋዜጠኛ ሮማነወርቅ ካሳሁንን እና የነፃነት ታጋዩን ማህተመ ጋንዲን ዘርዘር አድርገን እናስታውሳለን። ከዚያ በፊት ግን እንደተለመደው ሌሎች ዓለም አቀፋዊ ይዘት ያላቸውን የታሪክ ክስተቶች እናስታውስ።

ከ103 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥር 20 ቀን 1913 ዓ.ም ጀግናው ፀረ ፋሺስት አርበኛ ሌተናል ጀኔራል ጃገማ ኬሎ (የበጋው መብረቅ) ተወለዱ። ጃጋማ ኬሎ ሙት ዓመታቸው በሚታሰብበት የመጋቢት ወር ውስጥ በዝርዝር እናስታውሳቸዋለን።

ከ116 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥር 22 ቀን 1900 ዓ.ም ዳግማዊ አጼ ምኒልክ ኢትዮጵያ የዓለም አቀፍ የፖስታ ኅብረት (Universal Postal Union) አባል እንድትሆን ለኅብረቱ ደብዳቤ ፃፉ።

ከ131 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥር 25 ቀን 1885 ዓ.ም የንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ አጼ ምኒልክ አልጋ ወራሽ የነበሩትና ኢትዮጵያን ከ1903 ዓ.ም እስከ 1909 ዓ.ም ያስተዳደሩት ልጅ ኢያሱ ሚካኤል ተወለዱ።

ከ47 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት በዛሬዋ ቀን ጥር 26 ቀን 1969 ዓ.ም የደርግ ሊቀ መንበር የነበሩትን ብርጋዴር ጀኔራል ተፈሪ በንቲን ጨምሮ በኢ.ሕ.አ.ፓ ሰርጎ ገብነት የተጠረጠሩ የደርግ አባላትና የወዝአደር ሊግ (ወዝ ሊግ) ሊቀ መንበር የነበሩት ዶክተር ሰናይ ልኬ ተገደሉ። ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያምም ከድርጊቱ መፈፀም በኋላ ‹‹ለምሳ ሲያስቡን ለቁርስ አደረግናቸው›› አሉ።

አሁን በዝርዝር ወደምናያቸው የዛሬ ሳምንቱ በታሪክ ጀግኖችና ክስተቶች እንሂድ። የጋዜጠኛ ፍፁም ወልደማርያም ‹‹ያልተዘመረላቸው›› መጽሐፍ፣ አዲስ ዘመን ጋዜጣና የተለያዩ ድረ ገጾችን በዋቢነት ተጠቅመናል።

ጋዜጠኛ፣ ደራሲና ፀሐፊ ትውኔት ሮማነወርቅ ካሳሁን ከአባታቸው ከአቶ ካሣሁን እንግዳሸት እና ከእናታቸው ከወይዘሮ አለሙሽ ዓለም በ1914 ዓ.ም አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ተወለዱ። ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስም ቅድሥት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ገብተው የቤተ ክርስቲያን ትምህርት በመማር ዳዊት ደገሙ። ከዚያም ስዊድን ሚሲዮን ትምህርት ቤት በመግባት በጊዜው ይሰጥ የነበረውን ዘመናዊ ትምህርት ተማሩ። በትምህርት ቤት ቆይታቸውም የወቅቱን ‹‹ሴት ለትምህርት አልተፃፈችም›› የሚለውን ልማድ በጥረታቸውና በትጋታቸው በመቋቋም በትምህርት ቤት ቆይታቸው የአንደኛነት ደረጃን በመያዝ በአውሮፓውያን አስተማሪዎቻቸው ይሸለሙ ነበር።

በወቅቱ በነበረው ልማድም ገና በለጋ ዕድሜያቸው ትዳር ይዘው የአንዲት ሴት ልጅ እናት ሆነዋል።


ሮማነወርቅ በስዊድን ሚሲዮን ትምህርት ቤት ይማሩ በነበረበት ወቅት ከአውሮፓውያን መምህራን ያገኙት ዘመናዊ ትምህርት ከተፈጥሮ ችሎታቸው ጋር ተደምሮ በጥናትና ንባብ ያዳበሩትን እውቀታቸውን ወደ አደባባይ ማውጣት ስለፈለጉ በጥር ወር 1939 ዓ.ም በወቅቱ ‹‹የማስታወቂያና ፕሮፖጋንዳ ሚኒስቴር›› ተብሎ ይጠራ በነበረው መሥሪያ ቤት የመጀመሪያዋ ሴት ጋዜጠኛ በመሆን ተቀጠሩ።

በማስታወቂያ ሚኒስቴር ውስጥ በተሰጣቸው በሬዲዮ ጋዜጠኝነት ሥራቸው የተለያዩ ጽሑፎችንና ዜናዎችን በማዘጋጀት በማራኪ አንደበታቸው ሲያንቆረቁሩት በዜና አቀራረባቸውና በፕሮግራም ዝግጅታቸው በሕዝብ ዘንድ ከፍተኛ ተወዳጅነትንና አድናቆትን ለማግኘት ብዙም ጊዜ አልወሰደባቸውም ነበር።

ማስታወቂያ ሚኒስቴር ውስጥ ባገለገሉባቸው ጊዜያት በሬዲዮ ዜና አጠናቃሪነት፣ በዜና አንባቢነት፣ በሴቶች ፕሮግራም አዘጋጅነት ሠርተዋል። በወቅቱም ብዙ ፈተናዎችን ተቋቁመው በዝግጅቶቻቸው ላይ



ሮማነወርቅ ካሳሁን



ማህተመ ጋንዲ

የተለያዩ ማኅበራዊ ጉዳዮችን የሚዳስሱ ሥራዎችን በማቅረብ ሕዝቡን ሲያገለግሉ በትምህርት ገበታ ላይ ለነበሩት ሴቶች ልጆች እንደ ብርቅዬና የበጎ ተግባር ምሳሌ በመሆን ይታዩ ነበር። በዝግጅቶቻቸው የተለያዩ ወቅታዊ ርዕሰ ጉዳዮችን በማንሳት በወቅቱ በሴቶች ዘንድ ጫና የሚፈጥሩ አመለካከቶችን ለመፋቅ በመገናኛ ብዙኃን የራሳቸውንና የብዙ ሴቶችን ድምፅ አሰምተዋል።

የሴቶች ማኅበራዊ ሕይወት መሻሻል ላይ የሚያተኩሩ ጽሑፎችንም ይጽፉ ነበር። ከሥራዎቻቸው መካል የበኩር ሥራቸው የተጠናቀቀው በ1940 ዓ.ም ቢሆንም መጽሐፋቸውን ይዘው ወደ ሕትመት የሄዱት ግን ከሁለት ዓመታት በኋላ፣ በ1942 ዓ.ም ነበር። ይህንን ጉዳይ አስመልክተውም በመጽሐፋቸው መግቢያ ላይ እንዲህ በማለት ስለሕትመቱ ጉዳይ በትህትና ገልፀዋል።

‹‹ … መጽሐፌን ጽፌ የጨረስኩት በ1940 ዓ.ም ነበር። ከዚያ ወዲህ ሁለት ዓመታት ቆይቼ ሳነበው ከእርሱ የተሻለ ለመፃፍ የምችል ሆኖ ተሰማኝ። በዚህ ምክንያት ተሳንፌ ማሳተሙን ለማቆየት ከቆረጥሁ በኋላ የሰው እውቀት የዕድሜ ደረጃን ተከትሎ የሚሄድ እንጂ በአንድ ጊዜ አዋቂ አለመሆንን በማሰብ ዛሬ የተሻለ መስሎኝ ብሠራም ነገ መናቁ እንደማይቀር ተረዳሁት። ይህም የሰው አዕምሮ ያለማቋረጥ የሚሻሻል ለመሆኑ ዋና ማስረጃ ነው በማለት ይህን ሁሉ ካወጣሁና ካወረድሁ በኋላ ማመንታን ትቼ አሳተምሁት። … ››

የመጀመሪያ ሥራቸውን ለአንባቢ ያቀረቡት ወይዘሮ ሮማነወርቅ ለመጽሐፋቸው የመረጡት ርዕስ ‹‹ትዳር በዘዴ›› የሚል ነበር። መጽሐፉ የገጠሩንና የከተማውን ትዳርና ኑሮ የሚያነፃፅር ሲሆን በውስጡም በገጠር ያለውን የሕይወት ውጣ ውረድ ዘርዝሮ ያቀርባል። ከዚህ በተጨማሪም የመጽሐፉ ደራሲ ‹‹ለትዳር ፈላጊዎች ምክር አለኝ›› በማለት ስለትዳር የተለያዩ ጽንሰ ሃሳቦችን ለመዳሰስ ሞክረዋል። ሴቶች በማኅበራዊ ሕይወታቸው ውስጥ ያለባቸው ጫናም በመጽሐፉ ተዳስሷል። ከዚያ በኋላም በርካታ ጋዜጣ መጣጥፎችንና መጻሕፍትን ጽፈዋል። በሥራዎቻቸውም በርካታ ሽልማቶችን አግኝተዋል።

ጋዜጠኛ፣ ደራሲና ፀሐፊ ትውኔት ሮማነወርቅ የጤና እክል አጋጥሟቸው በሕክምና ሲረዱ ቆይተው ጥር 23 ቀን 1964 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። ሥርዓተ ቀብራቸውም በማግስቱ የማስታወቂያ ሚኒስቴር ሹማምንትና ሠራተኞች እንዲሁም እጅግ በርካታ ሕዝብ በተገኘበት አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በቀጨኔ መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ተፈጽሟል።

ጋዜጠኛዋ ሞት ቀደማቸው እንጂ ‹‹ሔዋን››፣ ‹‹መልካም እመቤት››፣ ‹‹የቤተሰብ አቋም››፣ ‹‹የባልትና ትምህርት››፣ ‹‹የሕፃናት ይዞታ››፣ ‹‹ዘመናዊ ኑሮ››፣ ‹‹የኑሮ መስታወት››፣ ‹‹ጋብቻና ወጣቶች››፣ እና ‹‹የባልና የሚስት ጠብ›› በሚሉ ርዕሶች መጻሕፍትን አዘጋጅተው ለሕትመት ለማብቃት እየጠበቁ እንደነበር ታሪካቸው ያሳያል።

### የነፃነት ታጋዩ ማህተመ ጋንዲ

የሕንዱ ማህተመ ጋንዲ የሙብት ተሟጋች ስለነበሩ በየትኛውም የዓለም ጫፍ ይታወቃሉ። በሀገራችን ኢትዮጵያም በተደጋጋሚ ስማቸው ይነሳል። ሆስፒታልም በስማቸው ተሰይሞላቸዋል።

ከ76 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥር 22 ቀን 1940 ዓ.ም የተገደሉትን ማህተመ ጋንዲን እናስታውሳቸው።

ማህተመ ጋንዲ የተወለዱት መስከረም 23 ቀን 1862 ዓ.ም (በአውሮፓውያኑ ኦክቶበር 2፣ 1869) ነው። ማህተመ ጋንዲ ‹‹የሕንድ አባት›› በመባል የሚታወቁ የሰላማዊ ትግል መሪ እና የፀረ ቅኝ አገዛዝ አብዮተኛ ናቸው።

‹‹ፍልስምና›› በተሰኘው የቴዎድሮስ ተክለ አረጋይ መጽሐፍ ላይ እንደተገለጸው፤ ጋንዲ እንግሊዞችን ፍጹም ሰላማዊ በሆነና ለእነርሱ ጨርሶ ሊገባቸው በማይችል እምነትና መንገድ የታገላቸው ነው። ከምዕተ ዓመታት ቅኝ ግዛታቸው ለማስወጣት የሕንድን ሕዝብ እያንቀሳቀሰ ስለሚፈታተናቸው ብዙ ጊዜ እስር ቤት ይከቱት ነበር።

ወደ መጨረሻው አስከፊ እስር ቤት በወረወሩበት ጊዜ ‹‹እናንተ አውሮፓውያን ወዳጆቼ ሆይ! የሰው ልጅ እኮ በአራት ግድግዳ የሚታሰር ግዑዝ ነገር አለዚያም እንስሳ አይደለም። የሰው ልጅ መንፈስ ነው። እዚህ በእስር ሳለሁ ጽናቱን እምነቴ ሕንዳውያን ወገኖቼን ያንቀሳቅሳል፤ እስር ቤት ክፉ የሚሆነው በመንፈስ ለታሰሩና በግድግዳ ለሚወሰኑ እውነተኞቹ እስረኞች እንጂ መንፈሳቸውን ከፍርሃትና ከጥላቻ ነፃ ላወጡ መንፈሳውያን እስራት አያስጨንቃቸውም፤ አያሸብራቸውም›› ብሏቸዋል።

በሌላ ጊዜ ደግሞ ጋንዲን የመጨረሻዎቹ ዱርዬዎችና ነፍሰ ገዳዮች መካከል ይከቱታል። ጋንዲ ወደዚያ ሲገባ ‹‹እነሆ ወንድሞቼ መሃል ገባሁ። ከዛሬ ጀምሮ የዚህ ቤተሰብ አካል ነኝ›› ይላቸው ነበር። ኀዘን ቢሰማው እንኳ ኀዘኑን በተስፋና በፍቅር ሊታገለው ይጀምራል እንጂ ቅሬታና ማጉረምረምን አያሰማም ይሉታል። በእነዚህ የማይጠቅሙ ተብለው በተጣሉ ዱርዬዎች ውስጥ ፍቅርና መልካምነት እንዳሉ ያውቃል ብቻ ሳይሆን ያምናል። እናም ኃላፊነት ይወስዳል። የእስር ቤቱን ቆሻሻ ማጽዳት ይጀምራል። እነዚያን አይጠቅሙም እንደውም ማኅበራዊ አደጋ ናቸው ተብለው የተጣሉ ነፍሰ ገዳዮችን በማክበር አክብሮት ከሚሰጠው መልካም ስሜት ያስተዋውቃቸዋል። ከእግዚአብሔር ያስተዋውቃቸዋል። ጤና አጠባበቅን፣ አብሮ መኖርን ያስተምራቸዋል። ታሪክ የማያውቁትን ታሪክ፣ ማይማኑን ማንበብ መፃፍ ያስተምራቸዋል። እንዲህ በመልካም ተግባር ተጠምዶ ሲውል ስለ እስር የሚያስብበት ጊዜ አልነበረውም። እንግዲህ ስለ ነፃነታቸው ሲል የራሱን ነፃነት ያጣላቸው ሕንዳውያን ማለት እነዚህን ወህኒ የተጣሉትንም እንደሚጨምር ያውቃል። እናም የብርሃን ተስፋውን በወህኒ ጨለማ ውስጥ ሳለ ይበልጡኑ ጸንቶና አምኖ እየታገለለት ነው ማለት ነው።

የትግሉ መንገድ ግን ጥላቻን በጥላቻ ማሸነፍ እንደማይቻል ጠንቅቆ ስለሚያውቅ ጥላቻን በፍቅር መፈተን ነው። ስለዚህ መታሰሩ አስጨንቆ ዓላማውን ጥሎ እጁን እንዲሰጥ አያስገድደውም። ይልቁንም በዚያ ጨለማ ውስጥ ሕይወትን ይጀምራል። እናም መታሰሩን ይረሳዋል። በዚህ ጊዜ እነሱው አሳሪዎቹ ራሳቸው አስታውሰው ነው የሚፈቱት። ‹‹የረገጥኳትን መሬት ለመባረክ ሥልጣን ተሰጥቶኛል›› ነው የሚለው።

ማህተመ ጋንዲ በዚህ የሕይወት መንገዱ ያስተማረኝ ትልቅ እውነት ‹‹በዙሪያህ የሚታይህን ክፋት መቋቋም ካቃተህ ‹እኔን ምን ነካኝ?› እንጂ ‹ዓለም ምን ነካት?› ብለህ አትጠይቅ›› የሚል ትምህርት ነው። እንዲህ ብለህ ብትጠይቅም መልስ አታገኝም። ዓለም ክፉ ናት ብትል ራስህ ክፉ ናት ካልካት ከዓለም በእጥፉ የከፋህ ትሆናለህ። በምትጠላው ነገር ውስጥ ያለውን መልካም ነገር የምታስተውልበት ዓይኖች ቢኖሩህ ክፉውን መልካም ታደርገዋለህ። እርሱን ፈውሰህ አንተም ትፈወሳለህ›› ይላል።

ማህተመ ጋንዲ በዚህ ባህሪው ራሳቸው እንግሊዛውያኑ ቅኝ ገዢዎች፣ ሙስሊሙ፣ ክርስቲያኑ፣ የሌላ እምነት ተከታዮቹ ሳይቀሩ ይወዱት፤ ይከተሉትና ያምኑት ነበር። እንግሊዞቹ ተብትበው በወጡት መከፋፈልና ጥላቻ ምክንያት በተፈጠረው እርስ በእርስ የመጠፋፋት ጦርነት ውስጥ ሙስሊሞቹ ሂንዱዎቹን እያባረሩ በቆንጨራ በሚጨፈጭፉ ሰዓት እንኳ ማህተመ ጋንዲን ግን ይሰሙት ነበር። ይከተሉት ነበር፤ እርሱ ዘንድ ሲደርሱ በፍቅሩ ጭካኔያቸውንና ቂም በቀላቸውን አሽንፎ ያንበረክካቸው ነበር።

የሁሉንም እምነት መጻሕፍት እየገለጠ በየዕለቱ ከሁሉም ሕንዳውያን ጋር አብሯቸው ይጸልይ ነበር። እናም ጋንዲ የቱንም መጥፎ የተባለን ቦታና ሃሳብ ወደ መልካም የመለወጥ ምሳሌ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። በመሸ ጊዜ ንጋትን በማሰብ ተስፋህን አምነህ ጉዞህን ጀምር የሚል እምነት አለው። የክፉ ነገር መጨረሻ ጥፋት ነው። መልካሙን የሚያመጣው የግለሰቦች ጽናት ነው። በመጨረሻው ጨለማ ውስጥ ወደ ብርሃንህ መመልከት የማህተመ ጋንዲ እምነት ነው።

ይህ የነፃነትና የሰብዓዊ መብት ታጋይ ናታሁራም ቪናያክ ጎድሴ በሚባል ግለሰብ በጥይት ተገድሏል። ገዳዩም የሞት ቅጣት ተፈርዶበት በስቅላት ተቀጥቷል። እነሆ የማህተመ ጋንዲ ስምና ሥራ ግን በዓለም ዙሪያ ሲወደስ ይኖራል።

### የፌስቡክ መፈጠር

ዘመን የየራሱ ትዝታ አለው። ይዞት የሚመጣው አዳዲስና አስገራሚ ነገሮች አሉት። እንደ ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ስልክ … የመሳሰሉ የመገናኛ ዘዴዎች ሲፈጠሩ ‹‹አጃዒብ›› አሰኝተው ነበር። ዛሬ ግን እነዚህ ሁሉ በሌሎች ፈጣን የመገናኛ ዓይነቶች እየተቀደሙ ናቸው። ከእነዚህ አንዱ ኢንተርኔትን መሠረት ያደረገው፣ ‹‹ፌስቡክ›› የተባለው የማኅበራዊ መገናኛ ዘዴ ነው። ፌስቡክ የራሱን አብዮት ፈጥሮ ታሪክ አስቀምጧል። ልክ በዛሬዋ ቀንና 20ኛ ዓመቱ መሆኑን ምክንያት በማድረግ በጥቂቱ እናስታውሰው።

ዓለምን እያሽከረከረ ያለው ‹‹ፌስቡክ›› የተባለው የማኅበራዊ መገናኛ ዘዴ ገና የ20 ዓመት ታሪክ ያለው ነው። ፌስቡክ የተገኘው የሀርቫርድ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በነበሩት ማርክ ዙከምበርግና ጓደኞቹ ከ20 ዓመታት በፊት ልክ በዛሬዋ ቀን ጥር 26 ቀን 1996 ዓ.ም (በአውሮፓውያኑ የዘመን ቀመር ፌብርዋሪ 4 ቀን 2004) ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ መተዋወቅ የጀመረው ግን ከ10 ዓመት አካባቢ በኋላ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ሲተዋወቅ ጥቂት ሰዎች ይጠቀሙት የነበረ ቢሆንም አብዛኛው ሰው መጠቀም የጀመረው ምናልባትም ከ2004 ዓ.ም አካባቢ በኋላ ነው።

ይህ ገና የ20 ዓመት ዕድሜ ያለው የመገናኛ ዘዴ አሁን ላይ ያሉ ታዳጊዎች ምናልባትም ብዙ ዘመን የቆየ ይመስላቸው ይሆናል። በተለይም በኢትዮጵያ ዓውድ ካየነው ደግሞ መረጃን በፍጥነት ማድረሱ ጥሩ ሆኖ ሳለ ለጥላቻና ለሀሰተኛ መረጃዎች መሰራጨት አሉታዊ ሚና አሳድሯል። ይህ ሲሆን ከ20 ዓመት በታች የሆኑ ታዳጊዎች ፌስቡክ ለብዙ ዘመናት የኖረ ይመስላቸው ይሆናል። ምክንያቱም እነርሱ ማገናዘብ የጀመሩበት ዕድሜ ላይ ሲደርሱ ፌስቡክ የሚባል ነገር አለ።

ከፌስቡክ በኋላ ብዙ የማኅበራዊ መገናኛ ዘዴ ዓይነቶች (ከመቶ ሰላሳ በላይ?) ቢመጡም የመጀመሪያው ግን ፌስቡክ ነውና እነሆ 20 ዓመታትን በማስቆጠር ታሪክ እያስመዘገበ ይገኛል።

ስፖርት እና መዝናኛ

# የዝነኞች ገጽ

## ባለክራሯ ድውር

ሙሉጌታ ብርሃኑ

ፒያሳ ጊዮርጊስ አፍ ቢኖረው፣ ዶሮ ማነቂያ ቢናገር፣ ደጃች ውቤም ቢመሰክር፣ ምናልባት ስለ ሜሪ አርምዴ ሳይሆን ሜሪ አርምዴን ዛሬም መልኳን ባሳዩን ነበር። እሷ እኮ የፒያሳ ድምቀት፤ የፒያሳ ጊዮርጊስ ጌጥ፤ የአዲስ አበባ ፈርጥ ነበረች። ክንፍ ባይኖራትም በሰማዩ ላይ ሳይቀር የምትበር፤ ባለክራር፤ የማትደክም ንስር አሞራ...የሕይወቷም ድውር ልክ እንደ ክራሯ ያለ ነበር። እያንዳንዱን አውታር በነኩት ቁጥር እንደሚሰጠው ልዩ ልዩ ዜማ። በአንድ ሕይወት ብዙ ድውር፤ በአንድ ክራር ብዙ ሙዚቃ አምባሰል፣ ባቲ፣ አንቺሆዬ እና ትዝታ የሕይወቷ መልክ ናቸው። ባለ ቅኔው በግጥም፤ ሌሎችም በቀለም በስዕል ይናገሩላታል። እንደ ቴዲ አፍሮ ያለው ደግሞ በሙዚቃው እንዲህ ይቀኝላታል፤

«ጸጉሯን ተተኩሳ እንደ አርምዴ ሜሪ፤

ዘመናይ ናት እሷ በክራር ነጋሪ»

ሲል ስላዜመላት ስለዚህች ምትሀተኛ እንስት ብዙ ሰምተን ይሆናል። በዛሬው የዝነኞች አምድ፤ የዝና ቅኝታችን ካሳለፈቻቸው የሕይወት ገጠመኞቿ ላይ ያደላ ይሆናል። ሜሪ የ40ዎቹና 50ዎቹ ምትሀት ነበረች። ከአንዲት መንደር ብቅ ብላ ሙሉ ትውልዱን ያንቀሳቀሰች ያነቃነቀች፣ ደግሞም ያስከተለች የዘመን አብዮተኛ ናት። ዛሬ ላይ ሆነን ይህቺን ምትሀተኛ ሴት ለማወቅ ወደ ኋላ መለስ ብንል፤ ሜሪ አርምዴ በብዙኃኑ ዘንድ፤ ስሟ እንጂ ሕይወቷ ተረስቶ ስለመኖሩ እንገነዘባለን። ዛሬ ላይ በመገናኛ ብዙኃንም ሆነ በብዕር ጠብታዎች፤ የሚወሳላት የሕይወት ታሪክና ገጠመኞቿ ከአንድ ቃለምልልስ ላይ የተገኙ ናቸው። ይህ የታሪክ ባለውለታም «መነን» መጽሔት ነበር። 1965ዓ.ም በጊዜው የዚህ መጽሔት አዘጋጅ ደግሞ ስብሐት ገብረእግዚአብሔር ነበር። እኔም፤ ብዕሬን እንዳነሳ አደረገኝ።

ልጅነት በሜሪ ሕይወት ውስጥ ከአብዛኞዎቹ የመንደሯ ልጆች የተለየ ነበር። እግሯ እሺ ብሎ ከአንድ ስፍራ የማይረግጥ፤ ሲልኳት እንደ በረሮ ቱር! ብላ ሄዳ የምትቀር እንደ ቁራ መልዕክተኛ ጭልጥ ባይ። ብዙ ወላጆች እንደሚሉትም «ቂጧ አርፎ የማይቀመጥ» ቅብጥብጥ ቀዥቃዣ፤ አንዳንዴም አይናፋር ቢጤ ነበረች። ሌላ አይደለም፤ እንዲህ የሚያደርጋት የሙዚቃው ውቃቢ ነው። ያክለፈልፋታል የሚለው ቃል እስከማይገልጻት ድረስ ቤተሰቦቿን ሳይቀር ፍዳቸውን ታበላቸው ነበር። ሜሪ መጥፎ አመል ኖሮባት አልነበረም፤ አመሏ ይኸው ሙዚቃ እና የሙዚቃ ፍቅር ነው። የሀገራችን የባህል ቁጥብነት ከሴትነቷ ጋር ተዳምሮ በማኅበረሰቡም ዘንድ ስክነትን የነፈጋት ልብ አውልቅ ተደርጋ እንድትታይ አደረጋት። ላይዋን እንጂ፤ እንዲህ ያገነፈላትን የውስጧን ወላፈን ያየ የተመለከተ አልነበረም። ጨዋታና ፍቅር ገበያ የወጡ ያህል በሚደራበት በዚያ የአራዳ መንደር ውስጥ፤ ጠጅ ቤቶች መደዳውን ይዘው ተገጥግጠዋል። የሜሪ ልብም ከቤቷ ይልቅ በመንደሯ ጠጅ ቤቶች አብዝቶ ይደሰታል። እግሮቿም የሚናፍቁት ወደዚያ ማምራትን ብቻ ነው። መላላክና መታዘዝንም የምትጠባበቀው በጉጉት ነው፤ ተልካ ስትወጣ ግን በስተመጨረሻ መገኛዋ እነዚሁ ጠጅ ቤቶች ናቸው። ይህቺ ታዳጊ ጠጅ አሊያም የሚንቆረቆር የጠጅ አንቡላ ናፍቋት አነበረም። ይልቅስ ጊዜዋን የምታጠፋው ከጠጅ ቤቶቹ መጋረጃ እያጮለቀች ሙዚቃ በመስማትና የአዝማሪዎቹን ክራር በማየት ነበር። ከጠጅ ቤቶቹ ውስጥ የሚታየው ሙዚቃዊ ትርኢት፤ ላይመልሰው ልቧን አሸፍቶት ነበርና በበርበሬና በአርጩሜም የምትመለስ አልሆነችም።

የሜሪ ቤተሰቦች የሚያደርጉት ጠፍቷቸው ትለወጣለች በማለት ከሚሲዮን ትምህርት ቤት አስገቧት። የያዛት መቸ በትምህርት የሚለቅ ሆነና፤ ይባስ ትምህርት ቤቱንም ማናወጥ ጀመረች። በቅጥር ግቢና ክፍል ውስጥ ሁሉ ማንጎራጎር ሥራዋ ሆነ። ይሄን የተመለከቱ መምህራኖቿም «ይች ልጅ ዘፈን እንጂ ትምህርት የሚሆናት አይደለችምና ሌሎች ልጆችንም እንዳታበላሽብን በሉ ተረከቡን» ሲሉ መልሰው አስረከቧት። ቤተሰቦቿም «ከእዚሁ ሆና ጫጩትም ቢሆን ትጠብቅ እንጂ ከቤት ውላ ልትለወጥ አትችልም» በማለት ዳግም ወሰዷት። በብዙ ልመናም ተመልሳ ገባች። ግን አሁንም ያው እራሷ ናት። ጓደኞቿ ከመጽሐፍትና ፊደላት ጋር ሲታገሉ፤ እርሷ ግን ከአንዱ ጥግ ሆና ይሄን ሙዚቃዋን ታንቆረቁረዋለች። በስተመጨረሻም፤ መነኩሴው የትምህርት ቤቱ አስተዳዳሪ «ከእንግዲህስ ዓይኗን እንዳላይ!» ሲሉ በቁጣ ሸኟት። እሷም «ግልግል!» ስትል ትምህርትን ዳግም ዞራ ላታየው ተሰናብታው ሄደች። ከዚህ በኋላ ሙሉ ጊዜዋን የምታሳልፈው ከጠጅ ቤቶቹ ጓዳና ሳሎን ሆነ። ተፈላጊና ተወዳጅ እየሆነች ከዚያው በክራር መዝፈኗን ቀጠለች። በዚህ መሀል ከአንዲት የፈረንሳይ ዜግነት ካላት ልጅ ጋር ተዋወቀች። ወዳጅነትና ፍቅራቸው ጠንቶ ከጓደኝነትም እንደ እህትማማች ሆኑ። ሜሪ የዘመኑን ብርቅዬና ተወዳጅ የሆኑትን ዘመናዊ ዳንሶችን ተማረች። በድሮዋ ሜሪ ላይ የዳንሱ ነገር ሲጨመርበት፤ ሀገር ምድሩ «ጉድ!» አለ። «ያን ጊዜ በውስጥ ሱሪና በጡት መያዣ፥ በባዶ እግር ነበር የሚደነሰው። ታዲያ ይህ ጉዳይ ኅብረተሰቡን አስቆጥቶት ነበር» ስትል ትገልጻለች። በዚህ መሀልም ፈረንሳዊቷ ጓደኛዋ ወደ ሀገሯ ስትመለስ የነበሯትን ንብረት በሙሉ ለሜሪ አስረክባ ሄደች። እዚህ ጋር፤ የሜሪ አርምዴ የአንድ ከፍታ ሁለተኛው የጉዞ ምዕራፍ መጀመሪያ ሆነ።

«ከዚያም አሁን የሞዳኖቫ ሱቅ ከተሠራበት የራስ ኃይሉ ንብረት ላይ ይገኝ የነበረ ቤት በከፍተኛ ገንዘብ ተከራየሁ። ችግሬ ግን የሠለጠኑ ሴቶች ማግኘቱ ነበር። እንዳሁኑ ሴቶች እኔው መርጬ አሠለጠንኳቸው። የፀጉር አሠራሩንም፥ ዳንሱንም አሠለጠንኳቸው። በዚያን ጊዜ ዳንሱም አለባበሱም ብርቅ ስለነበረ ገበያው ደራ» ትላለች። ሜሪ ሴቶችን የምታገኛቸው ወደ ጣሳ ቤቶች መንደር ጎራ በማለት ነበር። ቆነጃጅቱ ባላገር መሳይ ክራራቸውን ይዘው ከቺንኮ ተራ ከተፍ ይላሉ። ይህን መንደር ጣሊያኖቹ «ቺንኮ» እያሉ ሲጠሩት የአዲስ አበባው ሕዝብ ደግሞ «ከሰል ተራ» እያለ ይጠራዋል። የጣሳና ብርሌ፤ የጠጅና ጠላው፤ የክራር ሙዚቃው ኳኳታ የበዛበት መንደር መሆኑ ነው። እዚህ ሠፈር የሚረግጡት በብዛትም ኪሳቸው የነጣ፤ ኑሮ በዘዴዎቹ ናቸው። ሜሪ ከዚሁ ሠፈር ብቅ እያለች እኚያን ጉብል ኮረዳዎች ትጎበኛቸዋለች። ሴቶቹን ስመለከታቸው በጣም ነበር የሚያሳዝኑኝ የምትለዋ ሜሪም «ኑ እኔ ጋ ዳንሱን ተማሩ። እኔ ቤት ስንቱ እንግሊዝ፥ ስንቱ አሜሪካ፥ ስንቱ መኳንንት ይመጣል። እኔ ልውሰዳችሁ ስላቸው፤ እኛ ልብስ የለንም። አንቺ ጋ መጥተን ምን እንፈጥራለን? ሲሉኝ፤ ግድ የለም፤ የኔ ጌጥ የኔ ልብስ አለ፤ እያልኩኝ እወስዳቸው ነበር» በማለት በሁለት መንታ ስሜት ትገልጸዋለች። የወሰደቻቸውንም ሴቶች ጸጉራቸውን እየተኮሰች፤ ኩልን እየኳለቻቸው፤ ሁሉንም ነገር ከሀ እስከ ፐ አስተማርኳቸው የምትለው ሜሪ «ይኸውላችሁ እነሱኑ ለማሠልጠን ስል የፀጉር የመተኮሻውን ካስክ (ቆብ) እራሴ ላይ እያደረግሁ በሽተኛ ሆንኩ» ስትል ስለ መናገሯ ከመጽሔቱ ላይ ሰፍሯል።

በጊዜው የሜሪ አርምዴን ቡና ቤት የማይረግጥ ባለሀብት፤ ብቅ የማይል የውጭ ዜጋም ሆነ የሀገር ውስጥ አርቲስት አነበረም። የሚገርመው ደግሞ ከቡና ቤቱ የሚመጡትን እነዚህን ታላላቆች ለማየትና ለመገናኘት ሲል የሚመጣው ሰው ብዛት ደግሞ ጉድ የሚያስብል ነው። ጨለም ከማለቱ ገና «አልጀመረም? አርቲስቶቹስ ስንት ሰዓት ላይ ነው የሚመጡት?» እያለ በስልክ የሚያጨናንቃት ባለ ምጥ ብዙ ነው። ሦስት ሰዓት ላይ ለሚጀመረው የሜሪ ቡና ቤት የምሽት ዳንስ፤ ሁለት ሰዓት ከመሆኑ በፊት ቤቱ ከአፍ እስከ ገደፉ ጢም ብሎ ይፈሳል። የመቀመጫ ወንበር የማግኘቱ ነገር ከኪስ በላይ የሚያሳስብ ነው። ከቤቱ ጥግ ጥጉን ያቆመቻቸው የሰባቱ ወጠምሻ ጎረምሳ ግልምጫ ደግሞ ይባስ ለመቁነጥነጥም የማይሆን ነው። በመጠጥ ኃይል ተነሳስቶም ሆነ ተሳስቶ ለመደንፋት ያለውን አንጠልጥለው ያወጡታል። ሜሪ እንደሆን ዝናዋ ከአዲስ አበባ አልፎ፤ የበረራ ቲኬትም ሳይቆርጥ ሀገር አቋርጦ ያልደረሰበት አነበረምና ከውጭም መጣ ከውስጥ «ይህቺ ሜሪ የሚሏት የትኛዋ ናት?» እያለ በስም እየጠራ በዓይን የማይፈልግ፤ የማይጠይቅ አነበረም። እሷም በግልጽ ወጥታ ለመታየትም ሆነ በአካል ለመታወቅ አትፈልግም ነበር፤ ለምን? ስትባል «ምክንያቱም እኔን ለማየት ሲሉ ብቻ ገንዘባቸውን አውጥተው ቡና ቤቴን ስለሚጎበኙት ነዋ» ነበር ያለችው። አይ ሜሪ! ብቻ ሥራዋ ብዙ ነው።

ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ሲሆን በከተማው ብቸኛ የሆነው የሜሪ ቡና ቤት፤ በቀይ መብራት አሸብርቆ ቦግ እልም እያለ ጣሪያ ግርግዳውን ያሸበርቀዋል። ከወዲህና ወዲያ ብርጭቆውን እያነሳ «ቺርስ!» ይባባላል። ለሁሉም አዲስ በሆነው ባለቀለም መብራት፤ ከሜሪ ሴቶች ውበትና አርቲስቶቹ ጋር ተደማምሮ ከቤቱ የሚተነው እንፋሎት ሌላ ነው። እዚህ ጋር አንድ ነገር ትዝ አለኝ። ስብሐት ገብረእግዚአብሔር በ«ትኩሳት» መጽሐፉ ውስጥ ውቤ በረሃ እያለ የሚገልጸው ያ ስፍራ ምናልባትም ከሜሪ አርምዴ ቡና ቤት ውስጥ ሳይሆን እንዳልቀረ ጠረጠርኩ። ሜሪ በአዲስ አበባ ምድር ቡና ቤት ለመክፈትም ሆነ ባለቀለም መብራት ለመጠቀም የመጀመሪያዋ ናት። በኋላ ላይ ሜሪን የተመለከቱ ባለሀብቶች አንድ ሁለት እያሉ ቡና ቤት መክፈት ጀመሩ። እየተበራከቱም መጡ። በዚሁ መጠን ረብሻና ሁካታው በዛ። የማታ ማታ የከተማዋ አዳር፤ የውሻ መንጋ ሲናተፍ እንደሚያድርበት የቄራ መንደር መሰለ። በዚህ ጊዜ ሕጉም ጠበቅ አለና ክልከላው በዛ። ሴቶቹ ለብሰው የሚወጡት፤ በብዛት በውስጥ ልብሶች ብቻ ነበርና ይህ እንዳይሆን ክልከላ ተደረገ። በግለት የነበረው የሜሪ ቡና ቤት፤ ለመጀመሪያ ጊዜ ቀዝቀዝ ማለት ጀመረ። ብዙዎችም «ሜሪ ጥዩፍ ናት ... ሰው ትንቃለች፣ ትኮራለች...» እና መሰል የጎረምሶች ንዝንዝም፤ ዛቻና ማስፈራሪያ እየበዛበት መጣ። ሜሪም ከሁሉም ለመገላገል ስትል ቡና ቤቷን ዘግታ ቁጭ አለች። ያ ሁሉ ያጅባትና ሲጋፋላት የነበረ ሁሉ ጥሎ ጠፋ። ያሠለጠነቻቸው ቆነጃጅትም የራሳቸውን ቡና ቤት ከፍተው ባለሀብት ሆኑ። እርሷ ግን፤ ከስኬት ማማ ላይ ቁልቁል እየወረደች፤ ከአቧራው መሬት ላይ አረፈች። ዘውድና ጎፈር በአንድ የሕይወት ጆንበር። ገቢ ለማግኘት ስትል ጸጉር ቤት ከፈተች። በዚህም የመጀመሪያዋ በሆነችበት፤ በዘመናዊ የጸጉር ሙያዋ የአዲስ አበባን ሴት በሞላ አበባ ብታስመስልም፤ የእርሷ ሕይወት ግን ቁልቁል መምዘግዘጉን ሊያቆም አልቻለም።

በአንድ ወቅት የደቡብ አፍሪካዋ ማሪያም ማኬባ ለስብሰባ አዲስ አበባ በመጣችበት ጊዜ ‹‹ያቺን በዝና የሚወራላትን ሜሪ አርምዴን ሳላይ ወደ ሀገሬ አልመለስም›› በማለት ካለችበት ካላሳያችሁኝ አለች። ጋዜጠኞችም መርተው ቤቷ ድረስ ይዘዋት መጡ። ሜሪ የነበረችው፤ ድር ባደራበትና አቧራው ለአፍንጫ በሚሰነፍጥ ጉስቁልቁል ባለ ቤት ውስጥ ከአንዲት አልጋ ጋር ነበር። «እዚህ ቤት ውስጥ ነው የምትኖሪው?» አለቻት ማሪያ ማኬባ። «አይ፤ ይሄ የገረዴ ቤት ነው። ስለታመመችብኝ ልጠይቃት መጥቼ ነው» በማለት ትመልሳለች። ጉደኛዋ ሜሪ፤ ለካስ ሠራተኛዋን እንድትውንላት ለምና በማሳመን በብርድ ልብስ ጀቡና አስተኝታት ነበር። ከብርድ ልብሱ ስር ሆና ለጉድ ታቃስታለች። ሜሪም እንዲህ ነበር ያስታወሰችው፤ «እሷም እንዳልኳት ኧኧኧ ስትል ማርያም ማኬባ አዘነችና ሃምሳ የአሜሪካን ብር አንስታ «እንቺ ስጫት» አለችኝ። እኔም ያቺን ብር «የኔ ገንዘብ ነው በኋላ ትሰጭኛለሽ» ብዬ ትራስዋ ሥር አስቀመጥኩ። በኋላም ቤትሽን አሳይኝ ብትለኝ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ቲያትር አጠገብ ያለውን የበድሉን ሕንፃ የኔ ነው ብዬ ነገርኳት። ‹‹እናትና አባቴ ስለርስት ጉዳይ ንትረክ ይዘዋልና ፀጥታ እንነሳቸዋለን። እሁድ እራት ጋብዤሻለሁና እንዳትቀሪብኝ አልኩና ተሰናበትኳት። ግብዣውን የት አባቴ እንደማዘጋጅ ግራ ገባኝ። ምን ይዋጠኝ? ምነው ያችኑ አነስተኛ ቤት የኔ ነች ባልኩ፤ እያልኩ ስጨነቅ አንድ የማውቃቸውን ከፍተኛ ሥልጣን ያላቸውን ሰው ላስቸግር ወሰንኩ። እቤታቸው ሄጄ እግራቸው ላይ ወድቄ አለቀስኩ። ታሪኩንም ዘርዝሬ ነገርኳቸው። እሳቸውም በነገሩ ተደንቀው፥ ደግሰው፥ ቤቱን በደንብ አድርገው አዘጋጁልኝ። ከዚህም ሌላ ማርያም ማኬባን ከሆቴሏ የሚመጣት መኪናና ሾፌር ሰጡኝ። እኔም የእሳቸውንና የባለቤታቸውን ፎቶግራፍ ከግድግዳው ላይ አንስቼ የኔን ፎቶ አደረግሁ። የራሴ ቤት ለማስመሰል ፒጃማ ለበስኩ። ልክ እንደቤቴ ሽር ጉድ እያልኩ ጋበዝኳት። ሾፌሩንም አስቀድሜ ለምኜው ነበርና ከእራት በኋላ እሷን ለማድረስ ስንወጣ ወርዶ እጅ ነስቶ፥ መኪና ከፍቶ አስገባን። ሆቴሉም ስንደርስ ሮጦ ወጣና ከፈተልን። በመጨረሻም የሀገር ልብስ ጥሩውን በርካሽ ዋጋ ገዝቼ ሸለምኳት። እሷም ቆንጆ የደረት ጌጥ ሸለመችኝ። እባክህ ጌታዬ አታጋልጠኝ ብዬ ለቁልቢው ገብርኤል ጥላና ጧፍ ተስዬ ነበር። ሳልጋለጥ ቀረሁ» ይህን ማድረጓ፤ ይህችን ያህሏ ዝነኛ የምትኖረው በዚህ ቤት ነው ብላ የሀገሯን ስም በድህነት እንዳታጠለሽ ስለፈራች ነበር።

ሜሪ አርምዴ፤ በሁሉ የተሰጠች ናትና ማዘጋጃ ቤት ተቀጥራ ሴቶችን በዘመናዊ ፋሽን ማሰልጠን ጀመረች። ከዚያም ወደ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቴአትር ቤት አቅንታ በዚያም ለዘጠኝ ዓመታት ያህል ባላት ሙያ ሁሉ ስታገለግል ቆየች። የቴዎድሮስ ቴአትር ሲሠራ ሹሩባውን እንዲያ አሳምራ የሠራችው ሜሪ አርምዴ ነበረች። በሃኒባል ቴአትርም አልባሳቱን ያዘጋጀችው እርሷው ናት። በዚህ ሁሉ ግን አብዛኛውን ሥራዎች የምትሠራው በነፃ ነበር። ነገሮች እየከፉ ቀኑም እየጨለመ መጣ። በጭቃ ወደተመረገው ወደ አፈሩና ጭር ወዳለው ቤቷ ገብታ ቁጭ አለች። መከፋትና ድብርቱ ተጫጫኗት። ያላት ብቸኛው ነገር «ባሌም፤ አባቴም ወንድሜም እሱ ነው» የምትለው ያ ክራሯ ብቻ ነበር። በዥንጉርጉር ቀለም አጊጦ ከትራስጌዋ ተሰቅሏል። ሆድ ሲብሳት ከተሰቀለበት እያወረደች ብሶት መከፋቷን ትገልጽበታለች። ከፉኝ ብላ የምትነግረው የምታዋየው እንኳን አልነበራትም። ወዳጆቿ የነበሩትም ሜሪን የሚመለከቷት፤ ክራሯን ይዛ አንዳንዴ ከቴሌቪዥን መስኮት ብቅ ስትል ነው። ድምጽዋንም የሚሰሙት ከራዲዮን ላይ ስታንጎራጉር እንጂ ቤቷ ጎራ ብሎ የሚጠይቅ አነበረም።

«ዛፍ ያጣ ጉሬዛ አዳኝ ያበረረው የማትሆነኝ እንደሁ ልቤን ተው ልበለው

ጐጃምና ጐንደር ማዶ ለማዶ ነው ፍቅር ያለቦታው አባ ጨዳሬ ነው»

እያለች እንዳንጎራጎረች፤ ክራሯን ስትከረክር እንደኖረች፤ ኖራ ኖራ ከዚያው ደሳሳ ቤቷ አለፈች! ይህቺ ኦና ቤትም፤ ዛሬም ድረስ በፒያሳ ጊዮርጊስ ወገብ ላይ በትዝብት እንደቆመች አለች። እሷ ግን በክራር ጀመራ፤ በክራር ጨረሰች።



ሜሪ አርምዴ

# ዓለም አቀፍ

## የኑክሌር አረር ማስወንጨፊያ ሮኬት በአንድ አሜሪካዊ ግለሰብ ቤት ውስጥ ተገኘ

በጋዜጣው ሪፖርተር

የአሜሪካዋ ዋሽንግተን ግዛት ፖሊስ ከአንድ ግለሰብ ቤት የአሮጌ እቃዎች ማከማቻ ጋራዥ ውስጥ የተገኘው የዛገ ሮኬት የኑክሌር ሚሳኤል ማስወንጨፊያ መሆኑን አስታወቀ።

ባለፈው ረቡዕ በኦሃዮ ግዛት ቤልቩ ከተማ የሚገኝ ወታደራዊ ሙዚየም አንድ እምብዛም ያልተለመደ ስጦታ እንደተበረከተለት በመግለጽ ለፖሊስ ሪፖርት ማድረጉን ተከትሎ ነው ጉዳዩ ይፋ የሆነው።

ይህ እንደ ጦር ቅርስነት በስጦታ እንዲቀመጥ ሙዚየሙ እንዲወስደው የጠየቁት ግለሰብ ጥያቄ ግራ መጋባትን በመፍጠሩ፣ ፖሊስ ሪፖርቱ ከደረሰው በኋላ ቦምብ አምካኝ ቡድን ወደ ግለሰቡ ቤት ልኳል።

ፖሊስ ጉዳዩን አስመልክቶ ባወጣው መግለጫ የተገኘው ቁስ "አንድ ነጥብ አምስት ኪሎ ቶን የኑክሌር አረር መሸከም የሚችል ከአየር ላይ የሚተኮስ ሮኬት" መሆኑን በዝርዝር አመልክቷል።

ነገር ግን በሮኬቱ ውስጥ ሊተኮስ የሚችል የኑክሌር አረር አለመኖሩን በመግለጽ፣ በዚህም ሳቢያ በተገኘበት ስፍራ በሚገኝ ማኅበረሰብ ላይ ጉዳይ የሚያደርስ እንዳልሆነ አረጋግጧል።

የቤልቩ ፖሊስ መምሪያ ቃል አቀባይ የሆኑት ሴዝ ታይለር አርብ ዕለት ለቢቢሲ እንደተናገሩት፣ የተገኘው ቁስ "ለሮኬት ማስወንጨፊያነት የሚያገለግል ጋዝ ማከማቻ ዓይነት ነው።"

ጨምረውም የተገኘውን ነገር በተመለከተ "የቦምብ አምካኝ ቡድን አባላት ስለዚህ ቀፎ ብረት መግለጫ ማውጣት አስፈላጊ አይደለም ብለው ነበር" በማለት ጉዳዩ "ብዙም የሚያሳስብ አይደለም" ሲሉ አቃለውታል።

በአንድ ግለሰብ ቤት የተገኘውን የኑክሌር አረር አቃፊውን በተመለከተ ለፖሊስ ጥቆማ የደረሰው ዳይተን ኦሃዮ ውስጥ ከሚገኝ የአሜሪካ አየር ኃይል ብሔራዊ ሙዚየም ነበር።

ቁሱ በቤታቸው ውስጥ የተገኘው ግለሰብ ማንነት ያልተገለጸ ሲሆን፣ በመገናኛ ብዙኃን ለጉዳዩ በተሰጠው ሽፋን ምክንያት "በጣም መበሳጨታቸውን" የፖሊስ ቃል አቀባይ ተናግረዋል።

ግለሰቡ የኑክሌር ተሸካሚ ሮኬቱ ከይዞታ ሽያጭ ጋር የገዛው እና በሕይወት የሌለው ጎረቤታቸው ንብረት እንደሆነ ለፖሊስ አሳውቀዋል። በመጨረሻም ፖሊስ የተገኘውን ሮኬት "የፍንዳታ ጉዳትን የማያደርስ ቅርስ" በማለት ለይቶታል።

የኑክሌር አረር ተሸካሚው የማይፈነዳ እና ጉዳት የማያደርስ በመሆኑ የሀገሪቱ ሠራዊትም እንዲመለስለት



አልጠየቀም። ስለዚህ ባለበት ጊቢ ውስጥ ቆይቶ በሙዚየም ውስጥ ለዕይታ በሚቀርብበት ሁኔታ እንዲታደስ ፈቅዷል።

የመጀመሪያው እና ብቸኛው የዚህ የኑክሌር አስወንጫፊ ሮኬት የተተኮሰው እ.አ.አ. በ1957 ነበር። የሮኬቱ ምርት ደግሞ እ.አ.አ. መቋረጡን ዘገባው ጨምሮ ገልጿል።

## ቱርክ ለሞሳድ መረጃ አሳልፈው ሰጥተዋል የተባሉ ሰዎችን አሰረች

በጋዜጣው ሪፖርተር

የቱርክ የፀጥታ ኃይሎች ለእስራኤል የስለላ ተቋም ሞሳድ መረጃ አሳልፈው ሲሰጡ ነበሩ ያሏቸውን ሰባት ሰዎች በቁጥጥር ስር ማዋላቸው ተነገረ።

ሰባቱ ሰዎች በቁጥጥር ስር የዋሉት የቱርክ የደኅንነት ኤጀንሲ የሆነው ኤምአይቲ በኢስታንቡልና ኢዝሚር በተባሉት ከተሞች ውስጥ ድንገተኛ ዘመቻዎችን ካደረገ በኋላ ነው።

ቱርክ ከአንድ ወር በፊት ከሞሳድ ጋር ግንኙነት አላቸው ያለቻቸውን 34 ሰዎች በተመሳሳይ በቁጥጥር ስር አውላ ነበር።

የቱርክ ፕሬዚዳንት ረሲፕ ታይፕ ኤርዶዋን እስራኤል የሐማስ አባላትን ቱርክ ውስጥ ዒላማ ብታደርግ "ከፍተኛ መዘዝ" እንደሚጠብቃት አስጠንቅቀው ነበር።

ከመስከረም ማብቂያ ጀምሮ ከእስራኤል ጋር ጦርነት



ውስጥ የገባውን ሐማስን በርካታ ምዕራባውያን እና አረብ ሀገራት አሸባሪ ቡድንነት ቢፈርጁትም፣ ቱርክ ግን እዚህ ውሳኔ ውስጥ የለችበትም።

ከሞሳድ ጋር ግንኙነት አላቸው በሚል በቁጥጥር ስር ስለዋሉት ሰዎች የቱርክ መንግሥት እስካሁን ይፋዊ መግለጫ ባያወጣም፤ የቱርክ መገናኛ ብዙኃን ግን ሞሳድ የግል መርማሪዎችን ተጠቅሞ የሐማስ ቡድን አባላትን እንቅስቃሴ እንዲከታተሉና ፎቶግራፍ እንዲያነሱ ስለማድረጉ የሀገሪቱ የደኅንነት ተቋም ደርሶበታል ብለዋል።

ከአንድ ወር በፊት በቁጥጥር የዋሉት 34 ሰዎች "ፖለቲካና ወታደራዊ" ዓላማን ለማሳካት ለእስራኤል የደኅንነት ተቋም ስለላ በማድረግ ክስ እንደተመሠረተባቸው የቱርክ የፍትሕ ሚኒስትር ይለማዝ ቱነክ ተናግረው ነበር።

ሞሳድ የስለላ ተግባሩን እንዲፈጽሙለት በቱርክ ነዋሪ የሆኑ ፍልስጤማውያን እና ሶሪያውያን ሳይቀጥር እንደማይቀር ይገመታል።

የእስራኤል እና የሐማስ ጦርነት ከተጀመረ በኋላ የቱርኩ ፕሬዚዳንት ኤርዶዋን እና የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ቤኒያሚን ኔታኒያሁ የቃላት ጦርነት ውስጥ ገብተዋል።

ኤርዶዋን የጠቅላይ ሚኒስትር ኔታኒያሁን የጋዛ ወታደራዊ ዘመቻ "ዘር ማጥፋት" ብለው ከመግለጻቸውም በላይ ኔታኒያሁን ከናዚ ጀርመን መሪው ሂትለር ጋር አነጻጽረዋል።

እስራኤል በበኩሏ ከጋዛ በተጨማሪ በሊባኖስ፣ ኳታር እና ቱርክ የሚገኙ የሐማስ አባላትን ዒላማ እንደምታደርግ ስትዝት ቆይታለች።

መስከረም ወር 2016 ዓ.ም. የእስራኤል-ሐማስ ጦርነት መጀመሩ ይታወሳል። እስራኤል ለሐማስ ጥቃት እያካሄደችው ባለው የአጸፋ ምላሽ በርካታ ሰዎች መገደላቸውንና በጋዛ ከፍተኛ የሆነ የመሠረተ ልማት ውድመት ማጋጠሙን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አስታውቋል።

ፖስቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኃን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሠሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ጽሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## 24/7 የሚፋለሙበት...

ከ3ኛ ገጽ የዞረ

### እንደ መውጫ

የሳይበር ጥቃት በሚቀጥሉት ጥቂት አመታት እስከ ስድስት ትሪሊዮን ዶላር የሚደርስ ኢኮኖሚያዊ ጉዳት እንደሚያስከትል ጥናቶች አበክረው ይተነብያሉ። ከዓለምአቀፍ ሽብርተኝነት ባልተናነሰ የደህንነት ስጋት እስከ መደቀንም ደርሷል። ዓለም በሉላዊነት / ግሎባላይዜሽን / እና በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ወደ ትንሽ መንደርነት በተቀየረችበት የሳይበር ጥቃትና ጦርነት ለሀገራችንም ስጋት መሆን ከጀመረ ሰነባብቷል። በንግድ ባንክ በተደጋጋሚ የተቃጡ ጥቃቶቸ ፤ የፈተና ስርቆት በተማሪዎቸ ሥነ ልቦና እንዲሁም በጊዜያቸው ላይ ያስከተለው ጉዳት እንዳለ ሆኖ በሀገር ኢኮኖሚ እና በተቋማት አመኔታ ላይ ጥያቄ ማስነሳቱ አልቀረም።

የሳይበር ጥቃት በተደጋጋሚ የሚሰነዘር ቢሆንም መከላከል እንደሚቻል የዘርፉ ባለሙያዎች ይገልጻሉ። ሆኖም 99 በመቶ የሚሆኑ ድርጅቶች ለሳይበር ጥቃት የተጋለጡ ናቸው። የሀገራችን ተቋማት ይህን ተጋላጭነታቸው መቀነስ ላይ አበክሮ መሥራት ይጠበቅባቸዋል። በተለይ የደህንነት ፣ የፋይናንስ ፣ የኤሌክትሪክ ኃይልና የሚዲያ ተቋማት ልዩ ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

የሳይበር ጥቃት ዋና መከላከያ ዘዴ ከጫፍ ጫፍ ሁሉንም ኔት ወርኮች፣ ተንቀሳቃሽ ስልኮችንና የመረጃ መነሻና መዳረሻዎችንና ክላውዶችን ታሳቢ ያደረገ ተጋላጭነት የመቀነስ ሥራ መከወን ነው። ጠንካራ የሳይበር መከላከያ፣ ጥቃቱን መለየት ላይ ከማተኮር ይልቅ መከላከል ላይ በማተኮር፣ ጥቃት ሊቃጣባቸው የሚችሉ አሠራሮችን በመከላከል ፣ የመጨረሻውን ቴክኖሎጂ በመጠቀም እና ስለ ስጋት ምንጮች ወቅታዊ ግንዛቤ መጨበጥ ከዋና ዋናዎቹ የመከላከያ ዘዴዎች የሚጠቀሱ ናቸው። አበው እመው ነገርን ነገር ያነሳዋል እንዲሉ ስለ ሳይበር ጥቃት ከተነሳ አይቀር አኖኒመሶችን በስሱ ላስተዋውቃችሁ።

«ማንነታችን የማይታወቅ ወይም ስም አልባ አልያም አኖኒመስ ነን። ጭፍራ ነን። ይቅር አንልም ። አንረሳም ። ጠብቁን ።» መለያቸው ወይም ሞቷቸው ነው። ለማንም አይመለስም። የአሜሪካውን ግዙፍ የስለላ ተቋም ሲአይኤ ላይ ሳይቀር የሳይበር ጦርነት መክፈት የቻለ ኃይል ነው።

በራሽያው የደህንነትና የስለላ ተቋም ኤፍኤስቢ ላይም ተመሳሳይ ጥቃት ሰንዝሯል። የአሜሪካውን ኤፍቢአይና የእንግሊዙን ስኮትላንድ ያርድን ግንኙነት በተደጋጋሚ አስተጓጉሏል። ከሰሜን አትላንቲክ የጦር ቃል ኪዳን/ኔቶ/ መረጃዎችን ሰርስሮ የዘረፈ ሲሆን ዓለምአቀፉ የፖሊስ ተቋም ኢንተርፖል ላይም ተመሳሳይ የሳይበር ጥቃት ፈጽሟል።

ለማንኛውም ርዕዮተ ዓለም የገባ ወይም ያደረ አይደለም። ግራ ዘመም ሆነ ቀኝ አክራሪ ወይም መሐል ሰፋሪ አልያም ሊበራል ወይም ኮንሰርቫቲቭ አልያም ሶሻሊስት፣ ኮምኒስት ፣ ካፒታሊስት አይደለም ። ውግንና አለው ከተባለ ለእውነትና ለፍትሕ ነው ሲሉ ይመሰክሩለታል። የግፉአን እንባ አባሽ ነው የሚሉትም አሉ። መርሁ ጸረ ጭቆና ነው ሲሉ ሀክትቪስት ብለው የሚጠሩትም አሉ።


በትሩን የቀመሱ አገዛዞች፣ ተቋማትና ድርጅቶች ደግሞ የሳይበር አሸባሪ ነው ሲሉ ይከሱታል። የሰራዊቱ አባላት ከመላው ዓለም በበጎ ፈቃደኝነት የከተቱ ናቸው። ደመወዝ አይቆረጥላቸውም። ቀለብ አይሰፈርላቸውም። ትጥቃቸው የኮምፒውተር ቁልፍ ሰሌዳ /ኪይቦርድ/ እና የተካኑበት የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን እውቀት ነው። በሰው ልጆች ላይ በደል ፈጽሟል ያሉትን አገዛዝና ተቋም ወይም ድርጅት ላይ በኪይቦርዳቸው ያደባዩታል።

ባንኩን፣ የፋይናንስ ተቋሙን ፣ የኃይል ማመንጫውን ፣ መከላከያውን ፣ ደህንነቱንና ሌሎች ተቋማቱን ሽባ ያደርጉታል ። ሀገሩን ቀጥ ያደርጉታል። ያግቱታል። የመረጃ ቋቱን ሰርስረው ይገቡና/ሀክ ያደርጉና/መረጃ ይዘርፋሉ፣ ከጥቅም ውጪ ያደርጋሉ ፣ ያፋልሳሉ ፣ ያጠፋሉ ፣ በራሳቸው መረጃ ይተካሉ። ባልተለመደ ሁኔታ የሳይበር ጦርነትን በኦፊሴል በግልጽና በአደባባይ የሚያውጅ ብቸኛ የሳይበር ሰራዊት ነው።

ቀደም ባሉት ጊዜያት በአልቃይዳ፣ በአይኤስአይኤስ፣ በታሊባን ፣ በአልሻባብና በሌሎች ላይ የሳይበር ጦርነት ያወጀ ሲሆን በቅርቡ ደግሞ በራሽያ ላይ ጦርነት አውጇል። የራሽያ ፌዴሬሽንን የመከላከያ ሚኒስቴር የመረጃ ቋትን ሀክ አድርጎ ጥብቅ ወታደራዊ መረጃዎችን ዘርፏል። አጥፍቷል። አፋልሷል። ከጥቅም ውጪ አድርጓል። የራሽያን የቴሌቪዥንና የሬዲዮ ጣቢያዎችን ሀክ አድርጎ ስለዩክሬን የሚያቀነቅኑ መረጃዎችን እስከማስተላለፍና የዩክሬንን ብሔራዊ መዝሙር እስከማዘመር ደርሶ እንደነበር የእንግሊዙ «ዘ ኢንዲፔንዳንት» ጋዜጣ የቴክኖሎጂ አዘጋጅ ዳን ሚልሞ በዚያ ሰሞን ዘግቧል።

ሻሎም ! አሜን ።

# ስፖርት



## ለአፍሪካ ዋንጫ ክብር ያልታደሉ ኮከቦች

**ቦጋስ አበበ**

በተለያዩ ዘመናት በዓለም እግር ኳስ ትልቅ ተጽዕኖ ያሳደሩ በርካታ አፍሪካውያን ኮከቦች ተፈጥረዋል። ጥቂት የማይባሉ አፍሪካውያን በተለይም በአውሮፓ ታላላቅ ሊጎች ከሊግ ዋንጫዎች እስከ ቻምፒዮንስ ሊግ ድረስ በርካታ ክብሮችን ማሳካት ችለዋል። በክለቦቻቸው ስኬትም ቁልፍ ሚና ነበራቸው። እነዚህ ከዋክብት ከክለቦቻቸው ጋር ያላቸውን ስኬት ወደ ሀገራቸው ብሔራዊ ቡድን ተመልሰው በየሁለት ዓመቱ በሚካሄደው የአፍሪካ ትልቁ የእግር ኳስ ድግስ በድል መድመቅ የዘወትር ምኞታቸው ነው። ነገር ግን የብቃታቸው ጥግ ላይ በነበሩበት ዘመን ከክለቦቻቸው ጋር ያጣጣሙትን ስኬት ከብሔራዊ ቡድናቸውም ጋር የአፍሪካ ዋንጫን በማንሳት ስኬታማ የመሆናቸውን ያህል ያልተሳካላቸው ጥቂት አይደሉም። ከነዚህ መካከል በዘመናቸው ከአፍሪካ አልፈው ከዓለም ከዋክብት መካከል የሚጠቀሱ ነገር ግን የአፍሪካ ዋንጫን ማሳካት ሳይችሉ ጫማ የሰቀሉ ተጫዋቾችን እንመልከት።

**ዲዲየር ድሮግባ**

ኮትዲቯራዊው ኮከብ ዲዲየር ድሮግባ ዓለም ከማይረሳቸው ድንቅ አፍሪካውያን አጥቂዎች አንዱ ነው። ይህ ግብ አዳኝ ኮከብ በተለይም ከምዕራብ ለንደኑ ክለብ ቼልሲ ጋር ይህ ቀረህ የማይባሉ ስኬቶችን ማጣጣም ሲችል ለክለቡ ስኬታማ ዘመን ቁልፉ ተጫዋችም ነበር። ያም ሆኖ ቼልሲን ለተለያዩ ክብሮች ያበቃው ኮከብ ሀገሩ ኮትዲቯርን ለአፍሪካ ዋንጫ ክብር ለማብቃት እንደጓጓ ሳይሳካለት ነው ራሱን ከብሔራዊ ቡድኑ ለማግለል የተገደደው። ድሮግባ ከዝሆኖቹ ጋር የአፍሪካ ዋንጫ ህልሙን ለማሳካት ቀርቦ የነበረ ቢሆንም፣ እአአ 2012 ላይ በፍጻሜ ፍልሚያ በዛምቢያ ተሸንፎ በሚያስቆጭ ሁኔታ ዋንጫ ሳያነሳ ቀርቷል። የሁለት ጊዜ የአፍሪካ የዓመቱ ኮከብ ተጫዋች ሽልማት አሸናፊው ድሮግባ ራሱን ከብሔራዊ ቡድን ካገለለ ከሁለት ዓመት በኋላ (እአአ 2014) ግን ኮትዲቯር የአፍሪካ ዋንጫን ማንሳት ችላለች።

**ንዋንኮ ካኑ**

ከማይዘነጉ አፍሪካውያን ኮከቦች አንዱ የሆነው ናይጄሪያዊው ንዋንኮ ካኑ ድንቅ ተሰጥኦ ካላቸው ታሪካዊ ተጫዋቾች መካከል ይጠቀሳል። የአረንጓዴ ንስሮቹ ወርቃማ ትውልድ አካል የሆነው ካኑ በተለይም በሰሜን ለንደኑ ክለብ አርሰናል ያሳለፈው ድንቅ ዘመን ሁሌም አይረሳም። በአያክስ አምስተርዳም፣ በኢንተር ሚላን፣ በዌስት ብሮም እና ፖርትስማውዝ ባሳየው አስደናቂ ችሎታም በርካታ ክብሮችን አሳክቷል። እአአ በ1996 እና 1999 የአፍሪካ ኮከብ ሆኖ የተመረጠው ካኑ የአፍሪካ ዋንጫን ማንሳት ካልቻሉ የሚያስቆጩ ተጫዋቾች አንዱ ነው። ካኑ በአፍሪካ ዋንጫ ሀገሩ ናይጄሪያን 2000 ላይ ለፍጻሜ ከማብቃት የዘለለ ታሪክ መሥራት አልቻለም።

**አል-ሀጂ ዲዩፍ**

ዓለም ዋንጫን ጨምሮ በታላላቅ ውድድሮች ድንቅ ብቃት ማሳየት የቻለው ሴኔጋላዊ ኮከብ አል-ሀጂ ዲዩፍ አስገራሚ ተሰጥኦ ከታደሉ አፍሪካውያን ኮከቦች አንዱ ነው። ከአንዴም ሁለቴ የአፍሪካ የዓመቱ ኮከብ ተጫዋች ሆኖ የተመረጠው ዲዩፍ አስገራሚ የግል ችሎታው ሀገሩን የአፍሪካ ዋንጫ አሸናፊ ለማድረግ በቂ አልነበረም። 2002 ላይ ግን ቡድኑ ለፍጻሜ ቀርቦ በካሜሩን ተሸንፎ ህልሙን ሳያሳካ ቀርቷል።

**ማይክል ኢሴን**

ከቼልሲ ጋር ባሳለፋቸው ዓመታት ይበልጥ የሚታወቀው ናይጄሪያዊ ኮከብ ማይክል ኢሴን ከሰማያዊዎቹ ታሪካዊ ኮከቦች አንዱ ነው። 2006 ላይ የቢቢሲ የዓመቱ ኮከብ አፍሪካዊ ተጫዋች ሆኖ የተመረጠው ኢሴን ከአረንጓዴ ንስሮቹ ጋር የአፍሪካ ዋንጫን ማሳካት አልቻለም። ሀገሩን በ2010 የአፍሪካ ዋንጫ ለፍጻሜ ቢያበቃም በጋና አሸናፊነት ነበር የተጠናቀቀው።

**ጆርጅ ዊሃ**

ላይቤሪያዊው ታሪካዊ ኮከብ ጆርጅ ዊሃ የአፍሪካ ዋንጫን ማንሳት አለመቻል ከሌሎቹም በተለየ አስገራሚ ነው። በ1995 በኤሲ ሚላን ቆይታው ታላቁን የባሎን ድ ኦር ሽልማት በማሸነፍ ዛሬም ድረስ ብቸኛው ጥቁር ተጫዋች የሆነው ዊሃ ሀገሩን ግን ለአፍሪካ ዋንጫ ክብር ለማብቃት አልታደለም። ሁለት ጊዜ የአፍሪካ የአመቱ ኮከብ ሽልማት አሸናፊ መሆን የቻለው ዊሃ የሀገሩ ብሔራዊ ቡድን እሱ ከነበረበት የእግር ኳስ ከፍታ ጋር አብሮ መጓዝ የሚችል አልነበረም። በዚህም እንኳን የአፍሪካ ዋንጫን ለማንሳት በውድድሩ መሳተፍ የቻለውም በሁለት አጋጣሚ ብቻ ነበር። ይህም በ1996 እና 2002 ሲሆን ቡድኑ በሁለቱም ውድድሮች ከምድብ ጨዋታዎች ማለፍ አልቻለም።

**አሳሞሃ ጂያን**

ጋናዊው ኮከብ አሳሞሃ ጂያን በተጫወተባቸው የአውሮፓ ክለቦች ድንቅ ብቃት ከማሳየት ባሻገር፣ በዓለም ዋንጫ በርካታ ግቦችን በማስቆጠር ሪከርድ የጨበጠ ቀዳሚው አፍሪካዊ ተጫዋች ነው። 2010 ላይ የቢቢሲ የአመቱ ኮከብ አፍሪካዊ ተጫዋች የተሰኘው ጂያን በአፍሪካ ዋንጫ ዕድለኛ አልነበረም። ከጥቁር ከዋክብቱ ጋር 2010 እና 2015 ላይ ለአፍሪካ ዋንጫ ፍጻሜ ደርሶ በሁለቱም ሳይሳካለት ቀርቷል።

**ኢማኑኤል አዲባዮር**

ቶጓዊው ድንቅ ተጫዋች በአውሮፓ እግር ኳስ ከተለያዩ ክለቦች ጋር በርካታ ታሪኮችን መሥራት ቢችልም ከሀገሩ ብሔራዊ ቡድን ጋር የአፍሪካ ዋንጫን ለመሳም አልታደለም። 2006 ላይ ሀገሩን ለአፍሪካ ዋንጫ ሲያበቃ በማጣሪያ ጨዋታዎች 11 ግቦችን ከመረብ በማሳረፍ ኮከብ ሆኖ ነበር። ያም ሆኖ በውድድሩ ቶጎ ከምድብ ጨዋታዎች መሻገር ሳትችል ተሰናብታለች።

**ሙስጠፋ ሀጂ**

አፍሪካ ከማትረሳቸው ድንቅ ከዋክብት አንዱ የሆነው ሞሮኳዊው ሙስጠፋ ሀጂ በወርቃማ የእግር ኳስ ዘመኑ ከአትላስ አናብስቱ ጋር የአፍሪካ ዋንጫን አለማንሳቱ ያስቆጫል። 1998 ላይ የአፍሪካ የዓመቱ ኮከብ ተብሎ በተመረጠበት ዓመት እስከ ሩብ ፍጻሜ ብቻ የመጓዝ ታሪክ አኑሮ ነው ራሱን ከብሔራዊ ቡድኑ ያገለለው።

**ፍሬድሪክ ካኑቴ**

የማሊው ታሪካዊ ተጫዋች ፍሬድሪክ ካኑቴ 2007 ላይ የዓመቱ አፍሪካዊ ኮከብ ሽልማትን ተቀብሏል። ያምሆኖ አስደናቂ የእግር ኳስ ብቃቱን ባሳየባቸው ዓመታት ሀገሩን በ2004 የአፍሪካ ዋንጫ ግማሽ ፍጻሜ ከማድረስ የተሻገረ ታሪክ መጻፍ ሳይችል ነው የብሔራዊ ቡድን ማለያውን ያወለቀው።




## ልጆች እረፍቱን እንዴት እያሳለፋችሁ ነው?

**እየሩስ ተስፋዬ**



ሰላም ልጆችዬ፣ እንዴት ናችሁ? ሰላም ናችሁልኝ? «በጣም ደህና ነን። » እንደምትሉኝ ተስፋ አደርጋለሁ። ልጆችዬ፣ ትምህርታችሁን ስትከታተሉ የነበራችሁ ተማሪዎች የመጀመሪያውን መንፈቅ ዓመት፤ ወይም አንደኛ ሴሚስተር ፈተና ወስዳችሁ እንዳጠናቀቃችሁ ይታወቃል።

ልጆችዬ፣ ታዲያ ዝግጅታችሁ ምን ይመስል ነበር? ፈተናውስ እንዴት ነበር? ቀለላችሁ፣ ወይስ ከበዳችሁ? መቼም ልጆችዬ፣ ጥሩ ውጤት ለማምጣት ጊዜያችሁን በጥናት እና በንባብ እንዳሳለፋችሁ ምንም ጥርጥር የለኝም። ልጆችዬ፣ ሁልጊዜም እንደምንላችሁ ጥናት የሚጀመረው ፈተና ሲደርስ ብቻ አይደለም። ስለዚህም ሁሌም ማጥናት፤ ሁሌም ማንበብ ይኖርባችኋል።

አንዲት ጎበዝ ተማሪ እናስተዋውቃችሁ። ተማሪ ኑህሚን ከተማ ትባላለች። የአራተኛ ክፍል ተማሪ ናት። በትምህርቷ ጎበዝ ስትሆን ባለፈው ዓመት ሦስተኛ ደረጃን ይዛ ነበር ያጠናቀቀችው። ዘንድሮም የበለጠ ውጤት ለማምጣት በርትታ እያጠናች እና ትምህርቷን እየተከታተለች ትገኛለች።

እስካሁን በተፈተነቻቸው ፈተናዎች «ጥሩ» የሚባል ውጤት ለማምጣት ችላለች። ባሳለፍነው ሳምንት ፈተና ተፈትነው እንዳጠናቀቁ የምትናገረው ኑህሚን፤ እረፍቷን የተለያዩ መጻሕፍትን በማንበብ፣ አልፎ አልፎ ደግሞ ቤተሰብ በመርዳት በማሳለፍ ላይ እንዳለች ትናገራለች። ልጆችዬ፣ እናንተም እንደሷ እንዳቀዳችሁ፣ በእቅዳችሁ መሠረትም እያሳለፋችሁ እንደሆነ ተስፋ አደርጋለሁ።

ልጆችዬ፣ እረፍቱ አልቆ ወደ መደበኛ የትምህርት ገበታችሁ ተመልሳችሁ የፈተና ውጤታችሁን ስትቀበሉ የመጀመሪያ ሥራችሁ ሊሆን የሚገባው ምን መሰላችሁ? ራሳችሁን መመዘን። እንዴት ነበር ያጠናሁት? በክፍል ውስጥ የነበረኝ ተሳትፎ ምን ይመስላል? ለፈተና ያደረኩት ዝግጅት ምን ይመስላል? በማለት ራሳችሁን መጠየቅ አለባችሁ። ይህ ማሻሻል ያለባችሁን ነገር እንድታሻሽሉ ያግዛችኋል። በጣም ጥሩ ውጤት ባመስመዘገባችሁት የትምህርት ዓይነቶች ላይ ከዚህ በፊት ታደርጉትን የነበረውን የጥናትም ይሁን ትምህርታችሁን የምትከታተሉበትን መንገድ ማስቀጠል ይኖርባችኋል።

ጥሩ ውጤት ካላመጣችሁ ደግሞ ለምን ብላችሁ ጠይቁ። ስላልገባኝ ነው? መምህራን በክፍል ውስጥ ሲያስተምሩ ከልቤ ስላልተከታተልኩኝ ነው? ያልገባኝን ስላልጠየኩኝ ነው? ወይስ ፈተና ስፈተን መመሪያ እና ትዕዛዞችን በሚገባ ባለማንበቤ ተሸውጄ ነው? የሚሉትን እና ሌሎችን ጥያቄዎች በመጠየቅ ራሳችሁ መፈተሽ ይኖርባችኋል።

ሌላው ደግሞ ልጆችዬ፣ በትምህርታችሁ ጥሩ ውጤት ለማምጣት ከፈለጋችሁ ሁልጊዜ ከማጥናት ባሻገር መምህራን በክፍል ውስጥ ሲያስተምሯችሁ አጠገባችሁ ካለው ተማሪ ጋር ማውራት የለባችሁም። መረበሽም አያስፈልግም። እናም ልጆችዬ፣ በክፍል ውስጥ በንቃት መምህሮቻችሁ ምን ማስተማር እንደፈለጉ በንቃት በመሳተፍ፣ በመከታተል፣ ያልገባችሁን በመጠየቅ ማሳለፍ ይገባል።

በትምህርት ቤት ውስጥ ያላችሁን ትርፍ ሰዓት ደግሞ በጨዋታ ብቻ ከማሳለፍ ወደ ቤተ መጻሕፍት በማቅናት ብታጠኑ በትምህርታችሁ ውጤታማ ለመሆን ያግዛችኋል። በተጨማሪም ከትምህርት ቤት ጓደኞቻችሁ ጋር በጋራ በማጥናት እና ስለ ትምህርት በመጠያየቅ ማሳለፍ ይኖባችኋል።

ልጆችዬ ጥሩ ውጤት አላመጣሁም ብሎ መጨናነቅ ግን ተገቢ አይደለም። ከዚያ ይልቅ «እንዴት ላሻሽል?» ብሎ ማሰብ ያስፈልጋል። አንደኛ ሴሚስተር ወደ ሌላው ምዕራፍ እንድትሸጋሩ ዕድልን የሚሰጥ መሆኑን መቼም ታውቃላችሁ አይደል? እናም የዓመቱን ጥሩ ውጤት ለማምጣት በጥንካሬያችሁ መቀጠል ሲኖርባችሁ፤ ከድክመታችሁ ለመሻሻል ደግሞ የመምህራን፣ የወላጅ (አሳዳጊ)፣ እንዲሁም የእናንተ ድርሻ ከፍተኛ ነው።

ልጆችዬ፣ ለሁሉም ነገር ጊዜ፣ ወቅት እና ልክ አለው አይደል? «በትክክል» እንዳላችሁ ምንም ጥርጥር የለኝም። ስለዚህም እናንተ የምትገኙበት ዕድሜ የትምህርት መሆኑን በማሰብ ሙሉ ትኩረታችሁ ትምህርት እና ትምህርት ላይ ብቻ ማድረግ ይኖርባችኋል።

ሌላው ልጆች፣ በእረፍት ጊዜያችሁ ቴሌቪዥን፣ ታብሌት፣ ሞባይል እና መሰል ነገሮች ላይ ጊዜ የምታጠፉ ከሆነ በትምህርታችሁ ጥሩ ውጤት እንዳታስመዘግቡ እንቅፋት ይፈጥርባችኋልና ከዚህ ድርጊት ራሳችሁን አርቁ፤ እሺ ልጆች። ይህ ብቻ እንዳይመስላችሁ ልጆችዬ? በጤናችሁ ላይ ጉዳት የሚያደርስ መሆኑን በመገንዘብ ከእንዲህ ዓይነቶቹ፣ ጤናን ከሚጎዱ ነገሮች ራሳችሁን ማራቅ ይኖርባችኋል።

ወላጆች እና አሳዳጊዎችም ይህንን በመገንዘብ ልጆቻችሁ የእረፍት ጊዜያቸውን በንባብ፤ እንዲሁም ትምህርት ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር ይኖርባችኋል። በተጨማሪም ጥናት እና ሌሎች ነገሮች የሚከውኑበትን ሰዓት (ፕሮግራም) በማውጣት ልጆቻችሁ በእቅድ እና በፕሮግራም እንዲመሩ ያግዛቸዋል።

ከተቻለም በአካባቢ ወደ'ሚገኙ ቤተመጻሕፍት እንዲሄዱ በማድረግ የእረፍት ጊዜያቸውን በአግባቡ እንዲጠቀሙ ማበረታታት ያስፈልጋል። ይህ ደግሞ የተለያዩ እውቀቶችን እንዲያገኙ ያደርጋቸዋል። ታዲያ ከቦታ ቦታ ሲንቀሳቀሱ አደጋ እንዳያጋጥማቸው በጥንቃቄ እንዲሆን ከእናንተ እገዛ በተጨማሪ የሌሎችንም ርዳታ እንዲጠይቁ ማድረግ ይቻላል፤ ለምሳሌ የቤተመጻሕፍት ባለሙያዎችን።

ልጆችዬ ለዛሬው በዚህ እናብቃ አይደል? በአጠቃላይ ግን ፈተና ጨርሳችሁ አይደል? የሚኖራችሁን እረፍት በንባብ፣ ቤተሰቦቻችሁን በመርዳት፣ እንደ ሙዚቃ፣ ቴአትር፣ የፈጠራ ሥራ እና ሌሎች ችሎታ ካላችሁ ደግሞ እነሱን ለማዳበር እንደምትጠቀሙበት ተስፋ አደርጋለሁ። ልጆችዬ ሳምንት ደግሞ በሌላ ርዕሰ ጉዳይ እንደምንገናኝ ተስፋ በማድረግ፤ መልካሙን ሁሉ ለእናንተ እንመኛለን።